## የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ በሕግ ፡ ስለመጠበቅ ።

### በኤቨሬት ፡ ኤፍ ፡ ጎልድበርግ ።

የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ምንድን ፡ ናቸው? (የኢትዮጵያ ፡ ሕግስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የሚጠብቃቸው? የዚህ ፡ ማስታወሻ ፡ ዓላማ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከቱት ፡ የሕግ ፡ ክፍሎች ፡ በማጥናትና ፡ ስለአተረጓጐማቸው ፡ አስተያየት ፡ በማቅረብ ፡ እነ ዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ መመለስ ፡ ነው ። ስለመብት ፡ ማስከበርና ፡ አንድ ፡ ጥያቄን ፡ ወይም ፡ ክስን ፡ ከፍርድ ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋልም ፡ ባጭሩ ፡ ቀርቧል ።

የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክትን ፡ የሚጠብቁ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የዓለም ፡ ሕጐች ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ነው ፤ ከአገር ፡ አገርም ፡ የተለያየ ፡ ነው ። አግባብ ፡ ያላ ቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጥቂቶች ፡ በመሆናቸው ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ሁሉ ንም ፡ ችግሮች ፡ ካለመጥቀሱም ፡ ሌላ ፤ ለሚጠቅሳቸውም ፡ ችግሮች ፡ ሁሉ ፡ መፍትሄ ፡ አያቀርብም ። የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ዓላማ ፡ አጠቃላይ ፡ መፍትሔ ፡ ለመስጠት ፡ ሳይሆን ፡ ለውይይትና ፡ ለሃሳብ ፡ ልውውጥ ፡ መነሻ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ።

### የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ባሕርይና ፡ ሥራ ።

የንግድ ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ምን ፡ መሆናቸውን ፡ አይገልጹም ። በጠቅላላ ፡ አጠቃቀም ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ አባባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለአንድ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ለዕቃው ፡ አጠቃለል ፡ ወይም ፡ እንዱን ፡ ዕቃ ፡ በሌሎች ፡ አማካኝነት ፡ ከተሠሩት ፡ እቃዎች ፡ ለመለየትና ፡ ለማወቅ ፡ እንዲቻል ፡ ለማ ድረግ ፡ የሚጠቀምበት ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ። (ለምሳሌ ፡ በቢራ ፡ ጠርሙስ ፡ ላይ የሚገኘው ፡ ስም)[1] ። በአውሮፓ ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ተግባሮችን ፡ ይፈጽም ፡ ነበር ። አንደኛ ፡ የአንድ ፡ እቃ ፡ ባለ ቤትን ፡ ለይቶ ፡ ያስታውቃል ፡ ሁለተኛ ፤ የአንድ ፡ እቃ ፡ ልዩ ፡ ምንጭን ፡ ለይቶ ፡ ያስ ታውቃል ፡ (ለምሳሌ ፡ ሠሪውን ፡ ወይ ፡ ሻጩን) ፤ ይህም ፡ የአውሮፓን ፡ ንግድ ፡ የበ ላይነት ፡ ለነበራቸው ፡ የነጋዴዎች ፡ ማህበሮች ፡ (ጊልዳስ) ፡ ስለ ፡ እቃዎች ፡ ምንጮችና፡ ጥራት ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጐችና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እንዲችሉ ፡ በጣም ፡ አስፈ ላጊ ፡ ነው ።

---

1. የ"ንግድ ፡ ምልክት"ና ፡ የተመሳሳይ ፡ ቃላት ፡ ትርጉሞች ፡ እንደየአገሩ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ልዩነቶች ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አይጠኑም ። አንድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ምልክቶች ፡ የንግድ ፡ ስሞችና ፡ ስለማይገባ ፡ ውድድር ፡ (ኢንተርናሽናል ፡ የንግድ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፩) ፡ በተዘጋጀ ፡ የዓይነት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ በቁጥር ፡ ፩ ፡ የንግድ ፡ ምልክትን ፡ እንደሚከተለው ፡ ይገልፀዋል ፡-

   የአንድን ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ (የንግድ ፡ ዕቃዎች) ፡ ለመለየት ፡ ሲባል ፡ በንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋለ ፡ ወይም፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የታቀደ ፡ ማንኛውም ፡ ምልክት ፡ ነው ፡

   ቃላትን ፡ ስምን ፡ ሌሎች ፡ ዘዴዎችንም ፡ ጭምር ፡ ማናቸውም ፡ የመለያ ፡ ምልክት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሊያገለግል ፡ ይችላል ። ፩ሀ/ ኤፍ ፡ ሼክተር ፡ "ዘ ፡ ሂስቶሪካል ፡ ፋውንዴሽንስ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ሎው ፡ ሪሌቲንግ ፡ ቱ ፡ ትሬድማርክስ" (ኒውዮርክ ፡ የኮሎምቢያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ እትም ፡ ፲፱፻፳፭)ን ፡ ይመለከቷል ።

ምንም ፡ እንኳን እነዚህን ፡ ተግባሮች ፡ አሁንም ፡ ቢፈጽም ፡ ከዘመኑ ፡ የውድድር ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ዋናው ፡ ተግባሩ ፡ አንድ ፡ ደንበኛ ፡ አንዱን ፡ እቃ ፡ በዝና ፡ ወይም ፡ በልምድ ፡ በመመራት ፡ ለመግዛት ፡ እንዲረዳው ፡ እቃውን ፡ ከሌሎች ፡ እቃ ዎች ፡ ለመለየት ፡ እንዲያስችለው ፡ ነው ፤ በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሠሪ ፡ ወይም ፡ ሻጭ ፡ ገዢዎችን ፡ ለመሳብና ፡ ደንበኞችን ፡ ለመፍጠር ፡ የሚያስችለው ፡ ማለት ነው ። በዚህ ፡ አባባል ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የአንድን ፡ እቃ ፡ የተለየ፡ ምንጭ ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ ጠቅላላ ፡ ምንጭ ፡ ያመለክታል ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። አንድ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የሚያሳየው ፡ የዚህ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የሚገኝባ ቸው ፡ እቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ከሆነ ፡ ከአንድ ፡ ምንጭ ፡ መምጣታቸውን ፡ ነው ። እንደ ዚሁም ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቱ ፡ በገለልተኛ ፡ ሰው ፡ አስተያየት ፡ የሚመጠነውን ፡ ሳይ ሆን ፡ ገዢው ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በዝና ፡ ለእቃው ፡ የሚሰጠውን ፡ የጥራት ፡ ግምትን ፡ የሚያሳይ ምልክት ነው[2] ።

የአፍሪካና ፡ የማላጋሲ ፡ ኮንቬንሽንስ ፡ (ስምምነቶች) ፡ የትኞቹ ፡ ምልክቶች ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ሆነው ፡ ሊያገለግሉ ፡ መቻላቸውን ፡ ሊያስረዳን ፡ ይችላል ፡—

"የቤተሰብ ፡ ስሞች ፡ እንዳሉ ፡ ሆነው ፡ በልዩ ፡ ዓይነት ፤ ልዩ ፤ በፈጠራ ፡ ወይም ፡ በሀሳብ ፡ የተገኙ ፡ ስሞች ፤ የዕቃው ፡ ልዩ ፡ ቅድ ፡ ወይም ፡ አሠራር ፤ ምልክ ቶች ፤ ኤንቬሎፖች ፤ አትሞች ፤ ቴምብሮች ፤ ማኅተሞች ፤ ንድፎች ፤ የጠርዝ ፡ ጌጦች ፤ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ኅብር ፤ ሥዕሎች ፤ ቅርጾች ፤ መግሪያዎች ፤ የደራሲ ፡ የጽሑፍ፡ ስሞችና ፡ በጠቅላላው ፡ የአንድን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለመለየት ፡ የሚያስችሉ ፡ ምልክ ቶች ፡ ሁሉ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ይባላሉ ።"[3]

የአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ዋና ፡ ተፈላጊ ፡ ነገር ፡ ልዩ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ሌሎ ች ፡ አገሮች ፡ ይህን ፡ ተፈላጊ ፡ ነገር ፡ የያዙትንና ፡ ያልያዙትን ፡ ምልክቶች ፡ የሚለዩ፡ ብዙ ፡ ደንቦችን ፡ አደርጅተዋል ። ለምሳሌ ፡ ከሃሳብ ፡ የሚፈልቁ ፡ ስሞችና ፡ ከዕቃው ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸው ፡ ስሞች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የተለዩ ፡ ይሆናሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እቃውን ፡ የሚገልጹ ፡ ቃላቶች ፡ ወይም ፡ እቃውን ፡ ለመግለጽ ፡ በግድ ፡ የምንጠቀምባቸው ፡ ቃላትና ፡ ለተመሳሳይ ፡ እቃዎች ፡ የምንሰጠው ፡ አጠቃላይ ፡ ስም ፡ እንዲሁም ፡ በመጡበት ፡ ቦታ ፡ የምንሰጣቸው ፡ ስም ፡ ግን ፡ የተለዩ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ አይደሉም ። ስለዚህም ፡ "ጥሩ ፡" ወይንም ፡ "ቢራ ፡" የሚሉት ቃላት ፡ ብቻ ፡ ላንድ ፡ የቢራ ፡ ዓይነት ፡ የተለዩ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ። "አንበሳ ፡" የሚለው ፡ ግን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል[4] ።

---

2. ኤፍ ፡ ሼክተር ፡ "ዘ ፡ ራሽናል ፡ ቤዝስ ፡ ኦፍ ፡ ትሬድማርክ ፡ ፕሮቴክሽን ፡" ሃርቫርድ ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፵ ፡ (፲፱፻፳፮-፳፯)፡ ገጾች ፡ ፰፻፲፱-፰፻፴፫ በተጨማሪም ፡ ፒ፡ ሩቢየር ፡ "ለ፡ ድሮ ፡ ዴ ፡ ላ ፡ ፕሮፕሪዬቴ ፡ እንዱስትሪያል" ፡ (ፓሪስ ፡ ሲሬይ ፡ (፲፱፻፶-፶፩) ቮል ፡ ፪ ፡ ቁጥሮች ፡ ፪፻፶፪-፪፻፶፫ ፡ ሲ ፡ ጂ ፡ ዴ ፡ ሃን ፡ "ዘ ፡ ፕሮቴክሽን ፡ ኦፍ ፡ ትሬድ ፡ ማርክስ" ፡ ስለ ፡ "ሪስትሪክቲቭ ፡ ፕራክቲስስ ፡ ፓተንትስ ፡ ኤንድ ፡ ትሬድ ፡ ማርክስ ፡ ኤንድ ፡ አንፌር ፡ ኮምፒቲሽን ፡ ኢን ፡ ዘ ፡ ኮመን ፡ ማርኬት" ፡ መብቶች ፡ መጠበቂያዎች ፡ በንግድ ፡ ምልክቶችና ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ (ኢንተርናሽናል ፡ ኤንድ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፡ ክዋርተርሊ ፡ ሰፕሊሜንታሪ ፡ ፓብሊኬሽን ፡ ቁጥር ፡ ፬ ፡ ፲፱፻፷፪) ፡ ገጽ ፡ ፷ ።

3. ቁጥር ፡ ፪ ፡ እኔክስ ፡ ፪ ፡ የአፍሪካንና ፡ የማልጋሲን ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሀብት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚመለከት ፡ ስምምነት ፡ (፲፱፻፷፩) ፡ በኢ ፡ እፍነር ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ትሬድ ፡ ማርክ ፡ ፕሮቴክሽን ፡ (ኒውዮርክ ፤ ፊልድስትን ፡ ፕሬስ ፡ (፲፱፻፷፮) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፱ ።

4. የገዛ ፡ ስምን ፡ እንደንግድ ፡ ምልክት ፡ አድርጎ ፡ የመጠቀሙ ፡ ጉዳይ ፡ ሊያስከትል ፡ በሚችለው ፡ የተሳከረ ፡ ሁኔታና ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ለመጠቀም ፡ ባለው ፡ መብት ፡ መካከል ፡ በሚያስነሳው ፡ ግጭት ፡ ምክንያት ፡ ችግርን ፡ ሊያመጣ ፡ የሚችል ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ ፡ ፵፩ን ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ መጠቀምን ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁ ፡ ፵፯ንና ፡ የራስን ፡ ስም ፡ የንግድ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ ስለመጠቀም ፡ የንግድ ፡ ሕጉን ፡ ቁ ፡ ፪፴፯ን ፡ ይመለከቷል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ልዩ ፡ ያልሆነ ፡ ምልክት ፡ በመጠቀም ፡ ሕዝቡ ፡ ይህን ፡ ስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ እቃዎች ፡ ጋር ፡ የተገናኘ ፡ እድርጐ ፡ ከገመተ ፡ ይህ ፡ ምልክት ፡ ተፈላጊውን ፡ ልዩነት ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል[5] ። ሆኖም ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ልዩነቱን ፡ ሊያጣ ፡ ይችላል ፤ ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ተወዳጅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ ላንድ ፡ የተለየ ፡ እቃ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ተመሳሳይ ፡ ለሆኑት ፡ እቃዎች ፡ ጭምር ፡ መለያ ፡ ሆኖ ፡ ካገለገለ ፡ (ማለት ፡ "ሀ" ፡ የሚለው ፡ ፊደል ፡ ካንድ ፡ የቢራ ፡ ዓይነት ፡ ጋር ፡ መዛመዱ ፡ ቀርቶ ፡ በጠቅላላ ፡ ለቢራ ፡ ጥቅም ፡ ሲውል) ፡ ማለት ፡ ነው[6] ። ልዩ ፡ በሆኑና ፡ በሕግ ፡ መጠበቅ ፡ ባለባቸው ፡ ምልክቶችና ፡ ልዩ ፡ ባልሆኑት ፡ ምልክቶች ፡ ያለው ፡ መለያየት ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ ባለመሆኑ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሶችን ፡ አስከትሏል ።

በብዙ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ምልክቶች ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ሆነው ፡ እንዳይሠራባቸው ፡ ክልክል ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፡ አርማዎች ፤ ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፤ መለዮዎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡የመንግሥት ፡ ወይም ፡ በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ የተቋቋሙ ፡ የዓለምአቀፍ ፡ ድርጅቶች ፤ ወይም ፡ የሕዝብን ፡ ጸጥታና ፡ ሞራል ፡ የሚጐዱ ፡ ምልክቶች[7] ።

ሕጉ ፡ ለንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ የሚሰጠውን ፡ ጥበቃ ፡ ከማየታችን ፡ በፊት ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑትን ፡ ምልክቶች ፡ ለይተን ፡ እንወቅ ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ነጋዴ ፡ የሚነግድበት ፡ ስምና ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስሌዳ ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ። ነጋዴ ፡ የሚነግድበት ፡ ስምና ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፡ እንደ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የአንድን ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ክፍሉን ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ንግድ ፡ ለመለየት ፡ የሚያስችሉ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ከንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የሚለዩበት ፡ ነገር ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ የተወሰኑና ፡ የተዘረዘሩ ፡ ናቸው ። ነጋዴ ፡ የሚነግድበት ፡ ስም ፡ ማለት ፡ "ነጋዴ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኙትን ፡ ስምና ፡ የንግድ ፡ መደብሩንም ፡ ዐይነት ፡ ለይቶ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው"[8] ። በነጋዴው ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የራሱ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ከሃሳብ ፡

---

5. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ለዓይነት ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ ያወዳድሯል፦ የሚከተሉት ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ሆነው ፡ አይቆጠሩም ፦

(ሀ) የአንድን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ዓይነት ፡ መጠንና ፡ ብዛት ፡ ዓላማን ፡ ዋጋንና ፡ የጂኦግራፊ ፡ መሠረቱን ፡ (ማለትም ፡ የመጣበትን ፡ አገር) ፡ ለማመልከት ፡ በአጠቃላይ ፡ ሁኔታ ፡ የዋሉ ፡ ምልክቶች ፤

(ለ) ጥበቃ ፡ በሚፈለግበት ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ውስጥ ፡ የተለመዱ ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሕጋዊና ፡ የማይለወጡ ፡ የንግድ ፡ ልማዶች ፡ ውስጥ ፡ የተዘወተሩ ፡ በአጠቃላይ ፡ እኳኋን ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋሉ ፡ ምልክቶች ፤

ሐ/ በቁጥር ፡ ፭ ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ የመለያ ፡ ምልክቶች ፡ ያልሆኑ ። በእነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፤ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ይገባኛል ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ በእርግጥ ፡ የመለያ መሆኑን ፡ የማረጋገጥ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።

6. ኤስ ፡ ላደስ ፡ "ትራንስፎርሜሽን ፡ ኦፍ ፡ ኤ ፡ ትሬድማርክ ፡ ኢንቱ ፡ ኤ ፡ ጀኔሪክ ፡ ተርም ፡ ኢን ፡ ፎሬን ፡ ካንትሪስ "ዘ ፡ ትሬድማርክ ፡ ሪፖርተር ፡ ቮልዩም ፡ ፵ ፡ (፲፱፻፶፮) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፩ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ስለተወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ የተሰጠውን ፡ ማብራሪያ ፡ ይመለከቷል ። ዳግም ፡ ኢ ፡ አፍነር ፡ "ድራፍት ፡ ሞዴል ፡ ሎ ፡ ፎር ፡ ዴቬሎፒንግ ፡ ካንትሪስ ፡ ኦን ፡ ማርክስ ፡ ትሬድ ፡ ኔምስ ፡ ኢንድኬሽንስ ፡ ኦፍ ፡ ሶርስ ፡ ኤንድ ፡ አንፌር ፡ ኮምፒቲሽን ፡ እን ፡ አፕሬ ይዛል ፡ "ዘ ፡ ትሬድማርክ ፡ ሪፖርተር ፡" ቮልዩም ፡ ፶፮ ፡ (፲፱፻፶፰) ገጽ ፡ ፭፻፴፯ ።

7. ሞዴል ፡ ሎ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁ ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ።

8. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፸፩/፮ ። ሕጉ ፡ ስለንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሲናገር ፡ "የኩባንያ ፡ ስም" ፡ በሚል ቃል ፡ ተጠቅሟል ፡ ሆኖም ፡ የዚህ ፡ ጥቅም ፡ ከንግድ ፡ ስሙ ፡ ተግባር ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ቁጥሮች ፡ ፪፻፹ ፡ ፪፻፺፯ ፡ ፫፻፳፬ና ፡ ፭፻፲፬ን ፡ ይመለከቷል ።

የፈለቀ ፡ ስም ፡ ሲሆን ፡ ይችላል[9] ። የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፡ ማለት ፡ "የንግድ ፡ መደብር ፡ በሚከናወንባቸው ፡ ስፍራዎች ፡ ላይ ፡ የሚውል ፡ ስም ፡ ምልክት ፤ የንግዱ ንም ፡ መደብ ፡ ዓይነት ፡ ለይቶ ፡ የሚያስረዳ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው"[10] ። የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቱ ፤ ነጋዴው ፡ የሚነግድበት ፡ ስምና ፤ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳው ፡ አንድ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ሆኖም ፡ ሊለያዩም ፡ ይችላሉ ። ነጋዴው ፡ የሚነግድበት ፡ ስም ፡ እንዲሁ ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ሲሆን ፤ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳው ፡ በሚነግድበት ፡ ቦታ ፡ የሚለጠፍ ፡ ወይም ፡ የሚሰቀል ፡ ምልክት ፡ ነው ፤ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቱ ፡ ደግሞ ፡ ከሚሠራው ፡ እቃ ፡ ጋር ፡ የሚያያዝ ፡ ወይም ፡ የእቃው ፡ ክፍል ፡ ወይንም ፡ በጠቅላላው ፡ እቃውን ፡ የሚመለከት ፡ ነገር ፡ ነው ።

ሌሎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ስሞችም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡— ያገልግሎት ፡ ምልክት ፤ የሕብረት ፡ ወይም ፡ አጠቃላይ ፡ ምልክትና ፡ እቃው ፡ የተሰራበትን ፡ ቦታ ፡ የሚያሳይ፡ ማመልከቻ ። እነዚህም ፡ እንደ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የተወሰኑ ፡ አይደሉም ። ያገልግሎት ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ "አንድ ፡ ሰው ፡ የሚያቀርበውን ፡ አገልግሎት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ከሚያቀርቡት ፡ አገልግሎት ፡ ለመለየት ፡ የሚሆን ፡ ምልክት ፡ ነው"[11] ። ለምሳሌ ፤ ለጭነት ፡ በሚያገለግሉት ፡ መኪናዎች ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ስም ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የልብስ ፡ ንጽሕና ፡ መስጫ ፡ ባጠባቸው ፡ ልብሶች ፡ መሸፈኛ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ስም ፡ ያገልግሎት ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ። ያገልግሎት ፡ ምልክቶች ፡ በንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በመጠኑ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ከፍተዋል[12] ። የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ ለዕቃዎች ፡ እንደሚሰጡት ፡ ጥበቃ ፡ ሁሉ ፡ እነዚህ ፡ ያገልግሎት ፡ ምልክቶችም ፡ ለአገልግሎቶች ፡ ተመሳሳይ ፡ ጥበቃ ፡ ስለሚሰጡ ፡ ያንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶች ፡ አድርገው ፡ ያመለክቷቸዋል ። ሆኖም ፤ እኩል ፡ ጥበቃ ፡ አይሰጧቸውም[13] ። የማሕበር ፡ ወይም ፡ የትብብር ፡ ምልክት ፡ የሚባለው ፡ "አንድ ፡ ማኅበር ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ አማካኝነት ፡ የሚጠራ ፡ እቃ ፡ (ወይም ፡ እቃዎችን) ፡ ወይም ፡ የሚሰጥ ፡ አገልግሎት ፡ (ወይም ፡ አገልግሎቶች) ፡ የመነጨበትን ፡ ቦታ ፡ ለይቶ ፡ በማመልከት ፡ የሚጠቀምበት ፡ ምልክት ፡ ነው"[14] ። የዚህም ፡ ምሳሌ ፡ በአንድ ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር ፡ አማካኝነት ፡ የተሠሩት ፡ እቃዎች ፡ ላይ ፡ የሚያያዘው ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ እቃ ፡ ተፈላጊውን ፡ ደረጃ ፡ የያዘ ፡ ለመሆኑ ፡ የሚያስረዱ ፡ ምልክት ፡ ደረጃን ፡ በሚቆጣጠረው ፡ ድርጅት ፡ የሚለጠፈው ፡ ምልክት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ በሕግ ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ። የአገር ፡ ምንጭ ፡ ምልክት ፡ አንድ ፡ እቃ ፡ የት ፡ እንደተሠራ ፡ ያመለክታል ። ይህም ፡ በጣም ፡

9. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ ፡ ፩፻፴፮ ።

10. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁ ፡ ፩፻፵/፩ ። ዳግም ፡ "የሚነግድበት ፡ የተለየ ፡ የንግድ ፡ የማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፡" ተብሎ ፡ ይጠራል ፡ ቁጥሮች ፡ ፲፭/በ፲፰፰/፪(ለ) ።

11. ሞዴል ፡ ሎ ፡ ከላይ ፡ በማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ።

12. ደብልዩ ፡ ዳሬንበርግ ፡ "ትሬድ ፡ ማርክ ፡ ፕሮቴክሽን ፡ ኤንድ ፡ አንፌር ፡ ትሬዲንግ ፡ (አልባኒ ፡ ኒውዮርክ፡ ማቲው ፡ ቤንደር ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፯ ። ዳሎዝ ፡ ኢንሳይክሎፒዲያ ፡ ዡሪዲክ ፡ ሬፖርተር ፡ ደ ፡ ድሮ ፡ ኮሜርሲየል ፡ ኤ ፡ ዴ ፡ ሶስየት ፡ (ፓሪስ — ዳሎዝ — ቮልዩም ፡ ፪ ፡ ማርክ ። ደ ፡ ፋብሪክ ፡ ኤደ ፡ ሰርቪስ ፡ ቁጥር ፡ ፫) ። ኢ፡አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጾች ፡ ፪፻፳፰-፪፻፴፩ ፡ ይመለከቷል ።

13. ለዓይነት ፡ ሕግ ፡ የተዘጋጀው ፡ (ሞዴል ፡ ሎ) ፡ የአገልግሎት ፡ ምልክቶችን ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ምልክቶች ፡ አድርጐ ፡ ይቆጥራቸዋል ፡ ሞዴል ፡ ሎ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ና ፡ ገጽ ፡ ፰፩ ።

14. ሞዴል ፡ ሎ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ። ይህም ፡ በአንድ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ "የተመሰከረለት ፡ የንግድ ፡ ምልክት/ሰርተፊኬሽን ፡ ትሬድ ፡ ማርክ" ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፡ ለምሳሌም ፡ በ፲፱፻፴፯ቱ ፡ የኢንግሊዝ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፴፯ ፡ ሃልስበሪስ ፡ ስታትዩትስ ፡ ኦፍ ፡ ኢንግላንድ ፡ (ሁለተኛው ፡ እትም) ፡ ቮል ፡ ፳፭ ፡ ገጽ ፡ ፩፻ ፡ ፩፻፲፰ ።

አስፈላጊ ፡ የሚሆነው ፡ እቃው ፡ የተሠራበት ፡ ደረጃውን ፡ ወይንም ፡ ጠባዮችን ፡ የሚወስን ፡ ሲሆን ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡- በብዙ ፡ አገሮች ፤ በኢትዮጵያም ፡ ጭምር ፤ የሀሰት ፡ የቦታ ፡ ምንጭ ፡ ምልክት ፡ እንዳይሠራበት ፡ በሕግ ፡ ክልክል ፡ ነው ።[15]

አንዱ ፡ ነጋዴ ፡ የሌላውን ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክቱን ፡ የራሱ ፡ አስመስሎ ፡ ቢሠራበት ፡ ምን ፡ አለበት ? ሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ይህን ፡ አይፈቅድም ፤ ምክንያቱም ፡ በቦታው ፡ ነዋሪዎች ፡ መካከል ፡ ሚዛናዊና ፡ የቅን ፡ ልቦና ፡ ሥራን ፡ ለማዳበር ፡ ስለሚፈለግ ፡ ነው ። በንግድ ፡ መልክ ፡ የሚሠሩትን ፡ እቃዎች ፡ የሚገዙት ፡ ሰዎችም ፡ በመታለል ፡ ያልፈለጉትን ፡ እቃ ፡ ለመግዛት ፡ አይሹም ። ይህ ፡ እንዳይሆን ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ግን ፡ ነጋዴውን ፡ ነው ። የአንድ ፡ ንግድ ፡ ደህንነት ፡ የተመሠረተው ፡ በደንበኞቹ ፡ ላይ ፡ ነው ። አንድ ፡ እቃ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በሌላ ፡ እቃ ፡ ላይ ፡ ከሚገኘው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ጋራ ፡ ከተመሳሰለ ፡ አንድ ፡ ገዢ ፡ የሁለቱም ፡ እቃዎች ፡ ሠሪ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይገምት ፡ ይሆናል ። እቃዎቹ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ከሆኑ ፡ ግዥው ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ በሠሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እቃዎቹ ፡ ትንሽ ፡ ለየት ፡ ያሉ ፡ ቢሆኑም ፤ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ በደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ከሆነ ፡ የተሻለው ፡ ዕቃ ፡ ዝና ፡ ዝቅ ፡ ሊል ፡ ይችላል ።[16]

## በሕግ ፡ የንግድ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ጥበቃ ።

የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ እንደሚለው ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የመጠቀም ፡ መብትን ፡ የያዙት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቶች ፡ "በልዩ ፡ ሕጎች ፡" መሠረት ፡ ይተዳደራሉ[17] ። የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ የሚመለከት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ የለም ። ሆኖም ፡ አሁን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሕጎች ፤ ማለት ፡ በተለይም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፪ ፡ እና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፸፬ ፤ የአንድን ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የራሱ ፡ አስመስሎ ፡ ከሠራ ፡ ለተጐዳው ፡ ሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ መፍትሔ ፡

---

15. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ በተጠቀሰው ፡ ሞዴል ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፭ ፡ ውስጥ ፡ እንደሆነው ፡ ሁሉ ፡ ሐሰተኛ ፡ በሆነ ፡ ዕቃዎች ፡ የመጡበትን ፡ ስፍራ ፡ በሚያመለክት ፡ ጽሑፍ ፡ መጠቀም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያስቀጣ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፸፬ ፡ በግልጽ ፡ ተደንግጓል ።

16. የደንበኞችን ፡ መደናገር ፡ ከማስቀረት ፡ በስተቀር ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ የምልክቱን ፡ "ተውጦ ፡ መቅረት ፡ (ዳይሉሽን) ፡ የመከላከል ፡ ፍላጎት ፡ ይኖረዋል ። ስለ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ተውጦ ፡ መቅረት ፡ (ዳይሉሽን)" ፡ ከታች ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺ና ፡ ተያይዞ ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ይመለከቷል ።

17. የቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቅጅ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ፡- ቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡- የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ (ባለሀብትነት) ፡ መብቶች ፡ መጠበቂያ ፡-

(፩) የንግድ ፡ መደብር ፡ የተመዘገበ ፡ የመፈልሰም ፡ መብትን ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ ሥዕሎችንና ፡ ሞዴሎችን ፡ የሚመለከት ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

፪/ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቶች ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሥር ፡ ይውላሉ ።

በይበልጥ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነ ፡ የመጀመሪያው ፡ (ኦሪጅናል) ፡ የፈረንሳይኛውና ፡ የመደበኛው ፡ የአማርኛው ፡ ቅጅዎች ፡ "ፓተንትስ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ትርጉም ፡ "የኢንዱስትሪ ፡ ባለሀብትነት ፡" የሚለው ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ይኸው ፡ ትርጉም ፡ በቁጥር ፡ ፻፳፮/፪(መ) ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ "ፓተንትስ ፡" በሚለው ፡ ቃል ፡ ውስጥም ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ፡ ዳግም ፡ በቁጥር ፡ ፻፴፫/፩ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ "የተመዘገበ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚገልጸው ፡ የመፈልሰፍ ፡ መብት ፡ "የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንጅ ፡" የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ሥዕሎችና ፡ ሞዴሎች ፡ "የሚለውን ፡ ሐረግ ፡ አለመሆኑን ፡ ይገነዘቧል። ይህም ፡ በአማርኛውና ፡ በፈረንሳይኛው ፡ ቅጅዎች ፡ ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ቅጂ ፡ "ኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ ደ ፡ ል ፡ ኤምፓየር ፡ ዲ ፡ ኢትዮፒ ፡ ደ ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ (ፓሪስ ፡ ሊብሬር ፡ ጄኔራል ፡ ደ ፡ ድሮ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ዡሪስፕሩደንስ ፡ ፲፱፻፷፪) ነው ።

ይሰጣሉ[18] ። በተጨማሪም ፡ የንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የንግድ ፡ ምልክ ቶች ፡ መዝገብ ፡ እንድይዝ ፡ ይገደዳሉ ። በሕግ ፡ እንዲጠበቁ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ የለም ፤ ሆኖም ፡ ለዚህ ፡ ጥበቃ ፡ መዝገብ ፡ ማስፈለጉን ፡ የሚመለከት ፡ በቅርብ ፡ የተወሰነ ፡ ክስ ፡ አለ ።

### ፩/ የንግድ ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፤

የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩፻፴፪—፩፻፴፬ ፡ ተገቢ ፡ ባልሆነ ፡ የንግድ ፡ የውድድር፡ ሥራ ፡ የሚፈጸሙትን ፡ ጥፋቶች ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ የውድድር ፡ ሥራን ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የንግድ ፡ ምልክታቸው ፡ በማስመ ሰል ፡ ለተወሰደባቸው ፡ ሰዎች ፡ መፍትሔ ፡ እንደሚሰጡ ፡ ግልጽ ፡ ነው[19] ።

አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ደንበኞች ፡ እስካሉት ፡ ወይም ፡ እስኪኖሩት ፡ ድረስ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴ ፡ አማካኝነት ፡ "ደንበኛ ፡ ገበያተኛ ፡" የተባለ ፡ ዋጋ ፡ አለው ። በቅን ፡ ልቦና ፡ በተመሠረተ ፡ ውድድር ፡ የተነሣ ፡ የአንድ ፡ ነጋዴ ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተ ኞነት ፡ ሊቀንስ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፤ ተወዳዳሪዎቹ ፡ ከሱ ፡ የተሻለ ፡ እቃ ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ ለገበያ ፡ በማቅረብ ፡ ደንበኞቹን ፡ ሊወስዱበት ፡ ይችላሉ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የነጋዴው ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛነት ፡ የጠፋው ፡ ተወዳዳሪዎቹ ፡ አውቀው ፡ በፈ ጸሙት ፡ ተግባር ፡ ቢሆንም ፡ ይህ ፡ የተፈቀደ ፡ ነው[20] ። ነገር ፡ ግን ፡ የአንድ ፡ ተወዳዳ ሪን ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛነት ፡ የሚቀንሱ ፡ ተግባሮች ፡ ከአግባብ ፡ ውጭ ፡ ተብለው ፡ ስለሚቆጠሩ ፡ በሕግ ፡ የተከለከሉ ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ አነጋገር ፡ የንግድ ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ ጨዋታ ፡ ነው ። ተጫዋቾቹ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ መጫወት ፡

18. አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ እንቀጾች ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተገቢው ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ተጠቅሰው ፡ ይገኛሉ ፡ በተለዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ሊሠራባቸው ፡ የሚችሉት ፡ ቁጥሮች ፡ ግለጻ ፡ ከዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ አንጻር ፡ ውጭ ፡ ነው ።

19. የተለየ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕግ ፡ ቢኖርም ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጨማሪ ፡ መድኅን ፡ የሚሰጡ ፡ ይሆናሉ ፡ ለምሳሌ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕጉ ፡ በ፲፰፻፶፯ ዓ ፡ ም ፡ ከመሻሻሉ ፡ በፊት ፡ በንግድ ፡ ምልክት ፡ መመሳሰል ፡ የተጐዳ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡ ዘዴዎችን ፡ ሊከተል ፡ ይችል ፡ ነበር ። እንዚህም ፡ በተለየው ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ መመሥረት ፡ ወይም ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ የተመረከዘ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ነበሩ ። የተለዩት ፡ ሕጐች ፡ አግባብነት ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ በተመረኮዘው ፡ ክስ ፡ መጠቀም ፡ የሚቻል ፡ ሆኖ ፡ ሁለቱንም ፡ ክሶች ፡ መመሥረት ፡ ይቻላል ፡ ፒ ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀ ሰውን ፡ ፫ልዩም ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፶፮ን ፡ ይመለከቷል ። ወደ ፡ ሐሰት ፡ መለወጥንና ፡ አስተላልፎ ፡ መገኘ ትን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ሁለቱን ፡ የእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የክስ ፡ ሁኔታዎች ፡ በቲ ፡ ብላንኮ ፡ ሁዋይት ፡ ክርሲ ፡ ሎ ፡ እፍ ፡ ትሬድ ፡ ማርክስ ፡ ኤንድ ፡ ትሬድ ፡ ኔምስ ፡ (፱ኛው ፡ እትም ፡ ሎንደን ፡ ስዊት ፡ ኤንድ ፡ ማክስዌል ፡ ፲፱፻፷፭) ፡ ቁጥሮች ፡ ፩፻፺፪ና ፡ ፭፻፲፰ ፡ ውስጥ ፡ ያወዳድሯል ። ልዩ ፡ ሕግ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ የንግድ ፡ ምልክትን ፡ የሚመለከት ፡ ጠቅላላ ፡ መድኅን ፡ ሆኖ ፡ የመቆየቱ ፡ ጉዳይ ፡ በልዩው ፡ ሕግ ፡ ቃላት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ይሆናል ።

የንግድ ፡ ስምና ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ምልክቶች ፡ እንዳይገለበጡ ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ ድንጋ ጌዎች ፡ በግልጽ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገነዘቧል ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩፴፩/፪ ፡ ፩፴፫/፪ ፡ ፩፴፬/፪ ። በተጨማሪም ፡ ስለንግድ ፡ ምልክቶችና ፡ የማይረባ ፡ ውድድር ፡ ዶክተር ፡ ቡሐጅያር ፡ ቢአዛናው ፡ አለሜና ፡ በሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩምፓኒ ፡ ሊሚትድ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ በጸፋት ፡ የፍርድ ፡ ሀሳብ ፡ ላይ ፡ የሰጡትን ፡ ግሩም ፡ መግለጫ ፡ (ጠ.ን.ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፮) ፡ የኢት/ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ልዩም ፡ ፱ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፯ ፡ ላይ ፡ ይመለከቷል ።

20. ፒ ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ፫ል ፡ ፩ ፡ ቁጥሮች ፡ ፻፲፮ ፡ ፻፲፰ን ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ባሕረ-ሀሳብ ፡ ከመብቶች ፡ መተላለፍ ፡ ባሕረ-ሀሳብ ፡ የሚለይበትን ፡ በመግለጽ ፡ የተተፈውን ፡ ይመለከቷል ፡

አለባቸው ። የንግድ ፡ ጨዋታን ፡ የሚመለከቱት ፡ ሕጐች ፡ አብዛኛውን ፡ የሚገኙት ፡ የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራን ፡ በሚከለክሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ውስጥ ፡ ነው[21] ።

በቁጥር ፩፻፴፫ (፩) መሠረት ፡ የማይገባ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ በጠቅላ ላው ፡ "በንግድ ፡ ሥራ ፡ ከሐቀኝነት ፡ አደራረግ ፡ ውጭ ፡ የሚሠራው ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡" ነው ። በተለይም ፡ በቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ (፪) መሠረት ፡-[22]

"የማይገቡ ፡ የውድድር ፡ ሥራዎች ፡ ተብለው ፡ የሚቆጠሩትም ፡ በተለይ ፡ የሚ ከተሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) አንድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሚያወጣው ፡ እቃ ፡ ለማሳከር ፡ ሲባል ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የሚሠሩት ፡ የው ድድር ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው[23]" ።

የሚቀጥለው ፡ ውይይት ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ (ሀ) ን ፡ በተለይ ፡ የሚመለከት ፡ ቢሆንም ፡ የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፩) አማካኝነት ፡ የተሰጠ ውን ፡ ጠቅላላ ፡ አባባል ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። የማይገቡ ፡ የውድድር ፡ ሥራዎች ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (፪) ከተዘረዘሩት ፡ የተከለከሉ ፡ ተግባሮች ፡ ሌላ ፡ ተግባሮችን ፡ ያጠ ቃለለ ፡ ቢሆንም ፤ ለይቶ ፡ ለመወሰን ፡ ግን ፡ አዳጋች ፡ ነው ። ተገቢ ፡ ያልሆኑ ፡ የን ግድ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመወሰን ፡ የአንድ ፡ የንግድ ፡ አካባቢ ፡ ባሕሎችን ፡ መመልከትና ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የቶቹ ፡ ተግባሮች ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ እንደተሠሩ ፡ መወሰን ፡ ያስፈል ጋል[24] ። ይህም ፡ ሲባል ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ለቀረበለት ፡ ጉዳይ ፡ የሚቀርቡለት ፡ ማስረጃ ዎችን ፤ የዘመኑንና ፡ የአካባቢውን ፡ ሁኔታ ፡ አይቶ ፡ አመዛዝኖ ፡ ለመፍረድ ፡ መቻ ሉን ፡ ያስረዳናል ።

የሰውን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ እንደራስ ፡ አድርጐ ፡ መጠቀም ፡ "አንድ ፡ ተወዳ ዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሚያወጣው ፡ እቃ ፡" ላይ ፡ መሳሳትን ፡ ሊያስከትል ፡ ስለሚችል ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ (ሀ) ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ አግባብነት ፡ አለው ። እርግጥ ፡ ነው ፡ የማስመሰሉ ፡ ድርጊት ፡ መሳሳትን ፡ ለማ ስከተል ፡ በግድ ፡ በንግድ ፡ ምልክት ፡ መልክ ፡ መሆን ፡ የለበትም ። ይህ ፡ መሳሳት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ እንደራሱ ፡ መለዮ ፡ ወይም ፡ ምል

---

21. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፩ ።

22. "በተለይ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በፈረንሳይኛውና ፡ በአማርኛው ፡ የቁጥር ፡ ፩፻፴፫/፪ ፡ መግቢያ ፡ ሐረግ ፡ ቅጆዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ። የእንግሊዝኛው ፡ ቅጅ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጠቅላላ ፡ መንፈሱ ፡ ተመሳሳይ ፡ ውጤትን ፡ የሚያስገኝ ፡ ትርጉምን ፡ የሚጠይቅ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ አልያዘም ። ይህም ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ሥር ፡ ተዘርዝሮ ፡ ባይገኝ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ሆኖ ፡ ሊቆጠር ፡ መቻሉን ፡ ያሳያል ፡ ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ትርጉም ፡ ተለዋዋጭ ፡ በሆነው ፡ የንግድ ፡ ልማድ ፡ ውስጥ እንደልብ ፡ እየገባ ፡ ሊሠራበት ፡ ፡ የሚያ ስችለውን ፡ ደረጃ ፡ ይዟል ።

23. በቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠው ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ትርጓሜ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሀብትን ፡ ለመ ጠበቅ ፡ ተሻሽሎ ፡ ከወጣው ፡ ከ፲፰፻፹፫ ፡ የፓሪሱ ፡ ስምምነት ፡ (ከንቬንሽን ፡ ኦፍ ፡ ፓሪስ) ፡ ቁጥር ፡ ፲ለ ፡ ሁለተኛውና ፡ ሦስተኛው ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ መስመር ፡ ፩ና ፡ ፪ ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ። የመጀ መሪያ ፡ የሆነው ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ቅጅና ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲየል) ፡ የሆነው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ የዚህ ፡ ስምምነት ፡ ትርጉም ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ከተደረገው ፡ መሻሻል ፡ ጋር ፡ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ትሪትሲስ ፡ ኤንድ ፡ አዘር ፡ ኢንተርናሽናል ፡ አግሪመንትስ ፡ ቮል ፡ ፲፫(፲፱፻፷፪) ፡ ገጽ ፡ ፩(ቁጥር ፡ ፲/ለ/ ገጽ ፡ ፲፰ና ፡ ፴፯ ፡ ላይ ፡ ይገኛል) ፡ ላይ ፡ ታትመው ፡ ወጥተዋል ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ እንደሚያውቀው ፡ ከሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዚህ ፡ ስምምነት ፡ አባል ፡ አይደለችም ።

24. ፒ ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቮል ፡ ፩ ፡ ቁጥሮች ፡ ፺፲፬ ፡ ፺፲፰ ። እሱም ፡ በቁጥር ፡ ፺፲፬ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ የቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ ምንጭ ፡ በሆነው ፡ በፓሪሱ ፡ ስምምነት፡ ቁጥር ፡ ፲/ለ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኝ ፡ ያስገነዝባል ። (ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ን ፡ ይመለከቷል ።)

ክት ፡ አድርጐ ፡ ሲሠራበት ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ፤ ለምሳሌ ፡ እንደ ፡ ነጋዴው ፡ የሚነግድበት ፡ ስም ፤ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፤ ወይም ፡ ያገለግሎት ፡ ምልክት ፡ የመሳሰሉ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

የንግድ ፡ ምልክትን ፡ የራስ ፡ አስመስሎ ፡ መገልገል ፡ የሚያስከትለው ፡ ዋና ፡ አደጋ ፡ በደንበኞች ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ መሳሳት ፡ ነው ። አንድ ፡ ተግባር ፡ በሕግ ፡ ተጠያቂነትን ፡ የሚያስከትለው ፡ ደንበኞችን ፡ ሊያሳስት ፡ መቻሉ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ስለሚሆን ፡ ነው ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ በእርግጥ ፡ ሰውን ፡ ለማሳሳቱ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ለማሳሳት ፡ መቻሉን ፡ ለማስረዳት ፡ ቢረዳም ፡ የተሳሳቱትን ፡ ሰዎችን ፡ ማቅረብ ፡ ተፈላጊ ፡ አይደለም ። የዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ የፈረንሣዩ ፡ ትርጉም ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲተረጐም ፡ "በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ለማሳከር ፡ ሲባል ፡ የሚሠሩ ፡" ይላል[25] ።

አሁን ፡ ያለው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ትርጉም ፡ አንቀጹ ፡ ሊኖረው ፡ የታሰበውን ፡ ትርጉም ፡ የያዘ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ የተሻለው ፡ አተረጓጐም ፡ ነው። መሳከር ፡ መኖሩን ፡ በርግጥ ፡ ማስረዳት ፡ ቀርቶ ፡ መሳከር ፡ ሊደርስ ፡ መቻሉን ፡ ማሳየት ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ ከሳሹ ፡ ሊያስረዳ ፡ ማቅረብ ፡ የነበረበትን ፡ ከባድ ፡ የማስረጃ ፡ ግዴታን ፡ አቃልሎለታል ። በተጨማሪም ፡ የደንበኞች ፡ መሳከር ፡ መፈራቱን ፡ ደጋግሞ ፡ ያስታውሳል ። ይህም ፡ ተመሳሳይ ፡ ምልክቶችን ፡ በምንመረምርበት፡ ጊዜ ፡ መመጠኛ ፡ አድርገን ፡ መውሰድ ፡ የሚገባን ፡ ተራው ፡ ገዢን ፡ መሆኑን ፡ ያመለክተናል ።[26]

መሳከር ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ብለን ፡ ለመወሰን ፡ መገኘት ፡ ያለበት ፡ የመመሳሰል፡ መጠን ፡ በያንዳንዱ ፡ ሁኔታ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ትክክለኛ ፡ ግልባጭ ፡ ሲገኝ ፡ ሁልጊዜ ፡ መሳከር ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ምልክቶቹ ፡ በግድ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ መሆን ፡ እንደሌለባቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የተራው ፡ ገዢ ፡ ጠባይ ፡ ከሚገዛው ፡ እቃ ፡ ጋራ ፡ ተለዋዋጭ ፡ ሊሆን ፡ ቢችልም ፡ ቀኑን ሙሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምልክቶችን ፡ በማመዛዘን ፡ አያጠፋም ፤ ጥቃቅን ፡ ነገሮችን ፡ በቀላሉ ፡ ይረሳዋል ። እቃ ፡ ሊገዛ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን፡ ጥቃቅን፡ ክፍሎች ፡ ሳይመረምር ፡ ራሱ ፡ ሊመርጥ ፡ ይችላል ፤ ወይም ፡ ሻጩ ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ በጠቅላላ ፡ እንጂ ፡ ክፍል፡ በክፍል ፡ መመዛዘን ፡ እንደሌለባቸው ፡ ይስማማሉ ። ምልክቶችን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አቁሞ ፡ ልዩነቶችን ፡ መፈልግ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፤ ዳኛው ፡ ራሱን ፡ ዝንጉና ፡ አስተዋይ ፡ ባልሆነው ፡ ተራ ፡ ገዢ ፡ ቦታ ፡ አድርጐ ፡ መሳከር ፡ ሊኖር ፡ መቻሉን ፡ መወሰን፡ አለበት[27] ።

በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዳኞች ፡ በተለያዩ ፡ አመለካከት ፡ ተጠቅመዋል ። በአዛናው ፡ አለሜ ፤ ይግባኝ ፡ ባይና ፤ የሴንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፤

25. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የፓሪሱ ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፯ለ ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ፫ና ፡ ፭ ።

26. ኢ. ፡ አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፩፻፯-፩፻፲ ፡ ይመለከቷል ።

27. ከዚያው ፡ በዚህ ፡ ነጥብ ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ የአፍነር ፡ አስተያየት ፡ በልዩ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መሳከርን ፡ በሚያስከትል ፡ መመሳሰል ፡ ምክንያት ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ ምዝገባ ፡ ለማሠረዝ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ የሚደረገውን ፡ ክስ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የማይገባ ፡ ውድድር፡ በሚያስከትለውም ፡ መሳከር ፡ ውስጥ ፡ ሲሠራባቸው ፡ የሚቻል ፡ ይመስላል ።

መልስ ፡ ሰጭ[28] ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ምልክቶቹ ፡ የተሰሩት ፡ በአውሮፓውያን ፡ ካፒታል ፡ " S" በሚባለው ፡ ፊደል ፡ ዙሪያ ፡ ነበር ፤ የሴንቿር ፡ በፊደሉ ፡ ማሀል ፡ አንዲት ፡ ሴትዮ ፡ በመኪና ፡ ስትሰፋና ፡ በፊደሉ ፡ መስመር ፡ ላይ ፡ "የሴንቿር ፡ የስ ፌት ፡ መኪናዎች ፡" የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ፡ የአቶ ፡ አዛናው ፡ ደግሞ ፡ በፊደሉ ፡ ውስጥ ፡ የስፌት ፡ መኪና ፤ እላዩ ፡ ላይ ፡ ዘውድ ፡ ሲገኝ ፡ ከፊደሉ ፡ ቀጥሎ ፡ "ሳባ ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ መደብር ፡" የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ይገኛሉ ። እንደ ፡ ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሆነ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶቹ ፡ "አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰሉ ፡ መልካቸውና ፡ አሰራራቸው ፡ የተራራቀ ፡ ስለሆነ ፡ ማንንም ፡ ሊያሳስት ፡ የማይችል ፡ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ መለዮ ፡ ያላቸው ፡ምል ክቶች ፡" ናቸው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በምልክቶቹ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ልዩነት ፡ በጥብቅ ፡ ከማመኑ ፡ የተነሣ ፡ "ክሱን ፡ በሕግ ፡ አሳብቦ ፡ ወይም ፡ አስመስሎ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ተወዳዳሪውን ፡ ለማጥቃት ፡" የቀረበ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ገልጾ ፡ ከሳሹ ፡ ተከሳሹን ፤ "በማይ ገባ ፡ ክስ ፡ ባጉላላበት ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡" እንዲከፍል ፡ ፈርዶበታል[29] ። ዶክተር ፡ ቡሐጅያር ፡ የተለዩበትን ፡ የፍርድ ፡ አስተያየት ፡ ሲሰጡ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የተጠቀ ሙባቸው ፡ "S" የሚባሉ ፡ ፊደሎች ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ፈጽሞ ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ ነው ፡ (አይለያዩም) ፡" ብለዋል ። ሃሳባቸውንም ፡ በመቀጠል ፡ "ይሁንና ፡ ከነ ዚሀ ፡ ጥቃቅን ፡ ልዩነቶች ፡ በቀር ፡ በነዚህ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየ ውና ፡ ዓይን ፡ የሚማርከው ፡ ፊደል ፡ "ኤስ" ፡ ነው ። ይኸውም ፡ "ኤስ" ፡ "S" እና የስፌት ፡ መኪናውም ፡ ሲጨመር ፡ — መሳሳትንና ፡ ማሳከርን ፡ "ያስከትል ፡ ይሆናል፡ ብለዋል[30] ። በመጀመሪያ ፡ ክሱ ፡ በቀረበበት ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከሆነ ፡ የአቶ ፡ አዛናው ፡ ምልክት ፡ "በቀለሙ ፡ ሆነ ፡ በፊደሉ ፡ ቅርጽ ፡ ከአመልካች የንግድ ፡ ምልክት ፡ የተቀዳ ፡ ዓይነተኛ ፡ ግልባጭ ፡" ነው ፡ ብሎ ፡ ወስኖታል[31] ። እነዚህን ፡ ፍርዶች ፡ የሚለያቸው ፡ ዓይነተኛ ፡ ግልባጭ ፡" ነው ፡ ብሎ ፡ ወስኖታል ። እነዚህን ፡ ፍርዶች ፡ የሚለያቸው ፡ ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ እንደሚመስለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ በሚያወዳድርበት ፡ ጊዜ ፡ ጥቃቅን ፡ ክፍሎችን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ በቅርብ ፡ ማየት ፡ እንዳለበት ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነው ።

ስለ ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ "የንግድ ፡ ቤት ፡ (የ) ሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ (የ) ሚያ ወጣው ፡ ዕቃ ፡" መሳከር ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ እንድንችል ፡ እቃዎቹ ፡ የተመሳሰሉ ፡ ወይም ፡ የተገናኙ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። እቃዎቹ ፡ በተቀራረቡ ፡ መጠን ፡ ገዢው ፡ ወይም ፡ ደንበኛው ፡ ምንጫቸው ፡ ወይም ፡ ሠሪው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማሰቡ ፡ ይበ ልጥ ፡ እየተረጋገጠ ፡ ይሄዳል ፤ (ለምሳሌ ፡ በቢራና ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ ያለው ፡ ግንኙነ ትና ፡ በመኪናና ፡ በቢራ ፡ ያለውን ፡ ግንኙነትን ፡ አወዳድር)[32] ። በቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ መሠረት ፡ ነጋዴዎቹ ፡ ተወዳዳሪ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፤ ተወዳዳሪ ፡ ናቸው ፡ ለማለትም፡ በእቃዎቹ ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይነት ፡ እንዲኖር ፡ አሁንም ፡ ይፈ ለጋል ።

---

28. የጠ.ን.ነ. ፍ/ቤት ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል. ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፰ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በመለ ወጥ ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ።

29. የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፬ ።

30. የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፯ ።

31. የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፰ ።

32. የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ መመሳሰል ፡ ስለማመዛዘን ፡ በኢ ፡ አፍንር ፡ ክሳይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተ ጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፭፻-፭፲፫ ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ መግለጫ ፡ ይመለከቷል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ እቃዎቹ ፡ ጭራሽ ፡ የማይመሳሰሉ ፡ ቢሆኑና ፡ መሳከር ፡ ሊኖር ፡ ባይችልም ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ተጠቅሞበት ፡ "ስሙን ፡ ሊቀንስበት" ፡ ስለሚችል ፡ ይህን ፡ ለማስከልከል ፡ ይፈልግ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ። ይህ ፡ "ስም ፡ መቀነስ ፡" የሚለው ፡ አባባል ፡ የተመሠረተው ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የአንድ ፡ እቃ ፡ መለያ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ በታየ ፡ ቁጥር ፡ እቃውን ፡ ያስታውሳል ፡ በሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ ነው። ነጋዴው ፡ ተጠቀመ ፡ የሚባለው ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ የራሱን ፡ እቃ ፡ ለሰው ፡ ሲያስታውስ ፡ እንጂ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ እቃዎችን ፡ ሲያስታውስ ፡ አይደለም ። ምልክቱ ፡ ይበልጥ ፡ ከብዙ ፡ ሌሎች ፡ እቃዎች ፡ ጋራ ፡ በተዛመደ ፡ ቁጥር ፡ የነጋዴውን ፡ እቃ ፡ ማሳየቱ ፡ እየቀነሰ ፡ ይሄዳል ። በተጨማሪም ፡ ምልክቱ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ ላለው ፡ እቃ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ ልዩ ፡ ዓይነትም ፡ ቢሆን ፡ ሕዝቡም ፡ ያንን ምልክት ፡ ከዝቅተኛው ፡ እቃ ፡ ጋራ ፡ በማዛመድ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ ካላቸው ፡ እቃዎች ፡ ጋራም ፡ ያገናኘዋል ። በመጨረሻም ፤ ይህ ፡ "የስም ፡ ማደባለቅ ፡ ወይም ፡ መቀነስ ፡" የአንድ ፡ ምልክት ፡ ልዩ ፡ የመሆን ፡ ጠባዩን ፡ በመግፈፍ ፡ ይህ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ጥበቃ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማድረግ ፡ ሳያዳግት ፡ ወይም ፡ የማይቻል ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክትም ፡ በሕግ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ልዩ ፡ የመሆን ፡ ጠባይ ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ። መሳከር ፡ ሊደርስ ፡ ቢችልም ፡ ባይችል ፤ ይህ ፡ "ስም ፡ ማደባለቅ ፡ ወይም ፡ መቀነስ" የሚገጥመን ፡ ምልክቱ ፡ ባልሆነ ፡ እቃ ፡ ላይ ፡ በጥቅም ፡ ሲውል ፡ ስለሆነ ፤ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ "ስም ፡ ማደባለቅን ፡ ወይም ፡ መቀነስን ፡" ለማስቀረት ፡ ያለው ፡ ፍላጐት ፡ የሚረካው ፡ ተወዳዳሪው ፡ ነጋዴ ፡ የራሱ ፡ ባልሆነ ፡ ምልክት ፡ "ከመጠቀም ፡ ሲታገድለት ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ለቢራና ፡ ለአውቶሞቢሎች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ምልክት ፡ ቢሰጥ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ የሚያሳስት ፡ ሁኔታ ፡ እንደማይፈጠር ፡ ሁሉ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ መሳሳት ፡ አለመኖር ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ የሚረክስበትን ፡ ሁኔታ ፡ ያጠብበዋል ። ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ መራከስ ፤ አደናጋሪ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ የማይፈቅዱ ፡ ሆነው ፡ ቢታዩም ፤ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ አስተሳሰብ ፡ እምብዛም ፡ ተቀባይነትን ፡ አላገኘም[33] ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፹፫ ፡ ፪ (ሀ) ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ የንግዱ ፡ ምልክት ፡ አደናጋሪ ፡ መሆን ፡ ስላለበትና ፤ ውድድሩም፡ በተመሳሳይ ፡ ዕቃዎች ፡ መካከል ፡ እንዲሆን ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፤ ዕቃዎቹ ፡ የተለያዩ፡ ከሆኑ ፡ በቁጥር ፡ ፮፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ እንዳይረክሱ ፡ ለመጠበቅ ፡ አይቻልም ።

ከንግድ ፡ ምልክቶችና ፡ ከሚሠሩት ፡ ዕቃዎችም ፡ ጠባይ ፡ ሌላ ፡ ደንበኞችን ፡ የሚያደናግሩ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ። ለምሳሌ ፡ በይግባኝ ፡ ላይ ፡ አዛናው ፡ አለሜና ፡ በመልስ ፡ ሰጪ ፡ ሐላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የቤንዚር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ መካከል ፡ በነበረው ፡ ክርክር ፡ የማይገባ ፡ ተወዳዳሪ ፡ በመባል ፡ ክስ ፡ የቀረበበት ፡ ይግባኝ፡ ባይ ፡ የራሱን ፡ ሥራ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ የመልስ ፡ ሰጪ ፡ ተቀጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራ ፡ የነበረና ፡ ሥራውን ፡ ከጀመረም ፡ በኋላ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ ለጥፎ ፡ ሥራውን ፡

33. ኢ ፡ አፍንር ፡ ክላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፮ ። በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ ተውጦ ፡ የመቅረት ፡ ጽንሰ ፡ ሀሳብ ፡ ስለተሰጠ ፡ አስተያየት ፡ "ዲሉሽን ፡ ትሬድማርክ ፡ እንፍሪንጅመንት ፡ አርሂል ፡ ኦ ፡ ዘ ፡ ዊስፕ ፡" ሃርቫርድ ፡ ሎ ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፩፮ ፡ (፲፱፻፶፮) ፡ ገጽ ፡ ፬፻፭ ፡ ይመለከቷል ። በተጨማሪም ፡ ሼክተር ፡ ክላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ይመለከቷል ።

ያካሄድ ፡ የነበረው ፡ መልስ ፡ ሰጪው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ከመዛወሩ ፡ በፊት ፡ ይሠራ በት ፡ ከነበረው ፡ ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንኑ ፡ ተገን ዝቦ ፡ የሚያሳስት ፡ ነገር ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ፡ ሲል ፡ ፈረደ[34] ።

ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚኖረው ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ በሚፈጽሙት ፡ ተገቢ ባልሆነ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ተወዳዳሪዎች ፡ የሚባሉት ፡ ተመሳሳይ ፡ ደንበኞ ችን ፡ ለመሳብ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፡ በአንድ ፡ ገበያ ፡ ውስጥ ፡ እቃቸውን ፡ ለመ ሸጥ ፡ የሚሞክሩ ፡ ነጋዴዎች ፡ ናቸው ። ባሁኑ ፡ አነጋገር ፡ ይህም ፡ ሦስት ፡ ዐበይት ፡ ክፍሎችን ፡ ይይዛል ፤ ተወዳዳሪዎቹ ፡ ተመሳሳይ ፡ ውጤቶችን ፡ (ሸቀጦችን) በአንድ ፡ አካባቢ ፡ (ሥፍራ) ፤ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ መሸጥ ፡ አለባቸው[35] ። (፩) ጤፍ ፡ የሚያመርተው ፡ ሰው ፡ አውቶሞቢሎች ፡ ከሚሠራው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ አይደለም ። ሆኖም ፡ ውድድር ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ የሚሠሩት ፡ እቃዎች ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የተመሳ ሰሉ ፡ እንዲሆኑ ፡ አያሻም ። ጠጅ ፡ ጣይው ፡ ከቢራ ፡ ጠማቂው ፡ ወይም ፡ እንዲያውም አልኮልነት ፡ ከሌላቸው ፡ መጠጦች ፡ አዘጋጅ ፡ ጋር ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ ሊሆን ፡ ይች ላል ። (፪) በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ቢራ ፡ የሚሸጠው ፡ ሰው ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ቢራ ፡ ከሚሸጠው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ አይደለም ። ግን ፡ ውድድሩ ፡ የሚካሄድበት ፡ ሥፍራ ፡ የስፋት ፡ መጠን ፡ በተለይም ፡ በንግዱ ፡ ሥራ ፡ መጠን ፡ በሚያወጣው ፡ እቃ ፡ ዓይነትና ፡ ወደፊትም ፡ ደንበኞች ፡ ሊሆኑት ፡ በሚች ሉት ፡ ሰዎች ፡ አንፃር ፡ ሲታይ ፤ የተለያየ ፡ ይሆናል ። በእንቅስቃሴ ፡ ረገድ ፡ በሰዎ ችና ፡ በእቃዎች ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ለውጥ ፤ ውድድሩ ፡ ከየት ፡ ጀምሮ ፡ የት ፡ እንደሚ ያቆም ፡ ለመናገር ፡ በተለይም ፡ አስቸጋሪ ፡ ያደርገዋል ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ የቢራ ፡ ጠማቂ ፡ ቢራውን ፡ አስመራ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ቢሸጥና ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የቢራ ፡ ጠማቂ ፡ ደግሞ ፡ ቢራውን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ቢሸጥ ፤ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ሁሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ አይደሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ የንግድ ፡ ምልክ ትን ፡ በመቅዳት ፡ ረገድ ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ አይደሉም ፡ ማለት ፡ ስህተት ፡ ይሆናል ፡ በአ ሥመራና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መካከል ፡ በሚዘዋወረው ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ እየጨመረ ፡ በሄደ ፡ ቁጥር ፡ ተዘዋዋሪዎቹ ፡ ደንበኞች ፡ እቃው ፡ የት ፡ እንደተሠራ ፡ ግር ፡ ሊላቸው ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ አንዳንድ ፡ እቃዎች ፡ በአንዳንድ ፡ አካባቢ ፡ ውስጥ ፡ ተወዳጅነትን ፡ በማግኘት ፡ በቀላሉ ፡ አዲስ ፡ ገበያ ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችሉ ፡ መገን ዘብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ውድድሩ ፡ ሊሰፋፋ ፡ የሚችልበትን ፡ ሥፍራ ፡ በቅድሚያ ፡ ማወቅ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ መስፋፋት ፡ ረገድ ፡ ሊረዳ ፡ ይችላል ። በንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ረገድ ፡ ይህ ፡ የውድድር ፡ ክልል ፡ እስከ ፡ ሀገሪቱ ፡ ድንበሮች ፡ ድረስ ፡ መስፋት ፡ አለ በት ፡ ለማለትም ፡ ይቻላል[36] ።

ቢሆንም ፡ ይህ ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፡ በተለያዩ ፡ ሥፍራዎች ፡ የሚኖሩ ፡ በተመ ሳሳይ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ የሚጠቀሙ ፡ ነጋዴዎች ፡ ዕቃቸውን ፡ ለመሸጥ ፡ ከማቅረ ባቸው ፡ በፊት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባንድ ፡ አካባቢ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ደንበኞችን ፡ አዘጋ

34. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ የተጠቀሰው ፡ ጉዳይ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺፭ ። የጠ.ን.ነ. ፍ/ቤት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በሰወጠበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ ፍሬ ፡ ጉዳዮች ፡ አላብራራቸውም ፡ ፍር ዱንም ፡ የመሠረተው ፡ ምልክቶቹ ፡ የተለያዩ ፡ ስለሆኑ ፡ መሳከርን ፡ አያስከትሉም ፡ ብሎ ፡ ባመነበት ፡ ሀሳብ ፡ ላይ ፡ ነው ።

35. ፫ ፡ ላጋርድ ፡ "አንፌር ፡ ኮምፒቲሺን ፡ ፍራንስ" ፡ በኤች ፡ ኤል ፡ ፒንር ፡ የተዘጋጀ ፡ ወርልድ ፡ አንፌር ፡ ኮምፒቲሽን ፡ ሎ ፡ (ሊይድን ፡ ሲጅቶፍ ፡ ፲፱፻፶፮) ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፬፻፸፱ ፡ ይመለከቷል ፡

36. ብሔራዊ ፡ ወሰኖች ፡ በንግድ ፡ ምልክት ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትሉት ፡ ውጤት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ገጽ ፡ ፲፩ንና ፡ ፲፯ን ፡ ይመለከቷል ፡

ጅተው ፡ እንደሆን ፡ ችግር ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ምልክቱን ፡ እንዲለውጥ ፡ ወይም ፡ እንዲተው ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ። ለዚህ ፡ ችግር ፡ አንዱ ፡ መፍትሔ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ የጥፋተኝነትን ፡ መጠን ፡ የማመዛዘኑ ፡ አስፈላጊነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ተገልጿል ። (፫) የሽያጭ ፡ እቃ ፡ ማቅረብ ፡ ሥራውን ፡ ያቆመ ፡ ወይም ፡ ገና ፡ መሸጥ ፡ ያልጀመረ ፡ ሰው ፡ ያንን ፡ እቃ ፡ ከሚሸጥ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ አይደለም ። እዚህም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ አስቸጋሪ ፡ የአተረጓጎም ፡ ጥያቄዎች ፡ ሊነሱ ፡ ይችላሉ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ዕቃ ፡ ለመሸጥ ፡ ማቅረብን ፡ ወይም ፡ መሥራትን ፡ ለጊዜው ፡ ቢያቆምም ፡ ምልክቱን ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ እስከሚባልበት ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ እራሱ ፡ እስከሚተውበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ መጠበቅ ፡ የሚገባ ፡ ይመስላል ። እንዲሁም ፡ እቃውን ለመሸጥ ፡ ገና ፡ ገበያ ፡ ያላቀረበ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ይህንኑ ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳው ፡ ዘንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱንና ፡ እቃዎቹን ፡ ለሕዝብ ፡ በማስተዋወቅ ፡ ረገድ ፡ የወሰደው ፡ እርምጃ ፡ ካለ ፡ መብቱ ፡ በአእምሮ ፡ ግምት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ እስከሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ፡ ለማለትም ፡ ይቻላል ።[37] የውድድሩ ፡ ሐሳብ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ መጨመሩ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ምልክቱን ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ምልክት ፡ ጋር ፡ ለማሳከር ፡ እስከሚችልበት ፡ ደረጃ ፡ ድረስ ፡ የተመሳሰለ ፡ ከሆነ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ፈጽማሃል ፡ ተብሎ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆን ፡ አለበትን ? ወይስ ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንፈስ ፡ የሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ምልክት ፡ መኖሩን ፡ እያወቀ ፡ ያንን ፡ ምልክት ፡ በመቅዳት ፡ ደንበኞች ፡ በምልክቱ ፡ ተሳስተው ፡ ከተወዳዳሪው ፡ በመግዛት ፡ ፈንታ ፡ ከእርሱ ፡ ላይ ፡ እቃ ፡ እንዲገዙ ፡ አስቦ ፡ ያደረገው ፡ ለመሆኑ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበትን ? ወይስ ፡ አንድ ፡ ማዕከላዊ ፡ መንገድ ፡ አለ ? ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ ለእነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ የተሟላ ፡ መልስ ፡ አይሰጥም ። ቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ (፭) አንድን ፡ አድራጎት ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ታጣ ፡ ለማለት ፡ አድራጎቱ ፡ "ከሐቀኝነት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ አደራረግ ፡ ውጭ ፡ የሚሠራ ፡" እንዲሆን ፡ ይጠይቃል ፤ "ሐቀኛ" የሚለው ፡ ቃል ፡ ግልጽ ፡ ካለመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ የተለያየ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ። ቁጥር ፡ ፻፴፫ (፪) ስለ ፡ አእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ (ቅን ፡ ልቡና) ፡ አይናገርም ፤ ቢሆንም ፡ በቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ (፭) ውስጥ ፡ የሚመደቡ ፡ ልዩ ፡ ምሳሌዎች ፡ የያዘ ፡ በመሆኑ ፡ "በንግድ ፡ ሥራ ፡ ከሐቀኝነት ፡ አደራረግ ፡ ውጭ" የሚለው ፡ የመጨረሻ ፡ መለኪያ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚኖረው ፡ ይመስላል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ደንበኞችን ፡ (ገበያተኞችን) ፡ እርሱ ፡ የሚያቀርበው ፡ እቃ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲመስላቸው ፡ አስቦ ፡ ለማሳሳት ፡ ያደረገው ፡ ከሆነ ፡ ወይም ፡ አድራጎቱ ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑን ፡ አውቆና ፡ ይህንንም ፡ ውጤት ፡ ካስከተለ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ መፈጸሙ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የሠራው ፡ በንዝህላልነት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ ይህም ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ገበያተኞችን ፡ "ሊያሳስት ፡ እንደሚችል ፡ ያላወቁ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ማወቅ ፡ የሚገባው ፡ ከሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ከመሆን ፡ አያመልጥም ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ በመሠረቱ ፡ ሌላ ፡ (የእርሱን ፡ የሚመስል) የንግድ ፡ ምልክት ፡ መኖሩን ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ግን ፡ ሳያውቅ ፡ ሲቀር ፤ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ የሚያሳስት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አያሳስትም ፡ ብሎ ፡ ሲያምን ፤ ወይም ፡ የሌ

37. ልማዳዊ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ስለማውጣት ፡ ከታች ፡ ክፍል ፡ ፳፫ ፡ ይመለከቷል ።

ላው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕጋዊ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ሕጋዊ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ሲያስብ ፡ ነው ። በንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ የተመለከተ ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ በንዝህላልነት ፡ መሳሳት ፡ የሚችል ፡ ሁኔታን ፡ መፍጠር ፡ የሚያስከትለው ፡ ኃላፊነት ፡ (ጥፋተኛነት) ፡ የሚመነጨው ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ ለማስወገድ ፡ እቅዳቸው ፡ ከሆነው ፡ አናቅጽትና ፡ እነርሱም ፡ በሕጉ ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ ካላቸው ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ ነው ።[38]

የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ የሚከለከሉት ፡ ደንቦች ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ ውድድሩ ፡ በትክክል ፡ መካሄዱን ፡ ማረጋገጥ ፡ ነው ።[39] ይህም ፡ ዓላማ ፡ በደንብ ፡ ሊሟላ ፡ የሚችለው ፡ ታስቦ ፡ እንደሚደረግ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በንዝህላልነት ፡ የሚሠራ ፡ ድርጊትም ፡ የተከለከለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ነጋዴዎች ፡ የንግድና ፡ የመለያ ፡ ምልክቶቻቸውን ፡ በመምረጥ፡ ረገድ ፡ ብርቱ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ማበረታታት ፡ ያስፈልጋል ። አንድ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ ከብዙ ፡ የተለያዩ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ለመምረጥ ፡ የሚችል ፡ በመሆኑ ፡ ጥንቃቄ ፡ ይውሰድ ፡ ማለቱ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ አይሆንም ።

የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሚፈጸም ፡ ጥፋት ፡ ነው ።[40] ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚፈጠረው ፡ ጥፋተኝነት ፡ (ኃላፊነት) ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተዋል ። በቁጥር ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ መሠረት ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ለተፈጸመ ፡ ነገር ፡ ኃላፊነትን ፡ የሚያስከትለው ፡ ነገር ፡ ስህተት ፡ የሆነ ፡ ድርጊትና ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ራሱ ፡ ስህተት ፡ ባይሆንም ፡ በሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ለሚፈጸም ፡ ነገር ፡ ሐላፊነትን ፡ ያስከትላል ፡ የተባለ ፡ ድርጊት ፡ ነው ።[41] የማይገባ ፡ ውድድር ፡ በስህተት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ዓይነተኛ ፡ ጥፋት ፡ ነው ።[42] በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፳፱ ፡ (፩) ፡ መሠረት ፡ ስህተት ፡ "ሆን ፡ ተብሎ ፡ ወይም ፡ በንዝህላልነትና ፡ የተሠራ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።" ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ እጅ ፡ እልፊት ፡ ባሉ ፡ አንዳንድ ፡ ወንጀሎች ፡ አኅብቦ ፡ መሥራት ፡ (ሆን ፡ ብሎ ፡ ጉዳት ፡ ለማድረስ ፡ መሥራት) ፡ የወንጀሉ ፡ አካል ፡[43] ስለሆነ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻለው ፡ ጥፋት ፡ በአንድ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ቢሆንም ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ረገድ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ለሚለው ፡ አገላለጽ ፡ ግልጽ ፡ ወሰን ፡ አልተደረገለትም ። በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፶፯ ፡

38. ለምሳሌም ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በመጀመሪያ ፡ ለመጥፎ ፡ ሕሊና ፡ መኖር ፡ ማስረጃን ፡ ይጠይቁ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ቸልተኝነትን ፡ ማሳየት ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ቅን ፡ ልቡናም ፡ ቢሆን ፡ (ከኪሣራ ፡ በመለየት ፡) የማገጃ ፡ ትዕዛዝን ፡ ለማግኘት ፡ እስከሆነ ፡ ድረስ ፡ በቂ ፡ መከላከያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ዳሉዝ ፡ ኢንሳይክሎፒዲያ ፡ ንዑረዲክ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ኮንከሬንስ ፡ ደሎያል ፡ ኡ ፡ ኢሊሲት ፡ ቁጥሮች ፡ ፲፫-፲፪ ።
39. ፒ ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ።
40. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፪ ። የቁጥር ፡ ፻፴፪ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቅጂ ፡ የሚከተለውን ፡ ይናገራል ፡ "አንድ ፡ ነጋዴ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ መሠረት ፡ ከጥፋት ፡ የሚቆጠር ፡ የውድድር ፡ ሥራን ፡ ፈጽሞ ፡ ከተገኘ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችላል ።" በይበልጥ ፡ ትክክል ፡ የሆነው ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ትርጉም ፡ "አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ከጥፋት ፡ የሚቆጠር ፡ የውድድር ፡ ሥራን ፡ ፈጽሞ ፡ ከተገኘ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ኃላፊነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ መሠረት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ፡" የሚል ፡ መሆን ፡ አለበት ፡
41. የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቅጅ ፡ "ፎ" ፡ የሚለውን ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቃል ፡ "ኦፈንስ" ብሎ ፡ ይተረጉመዋል ። የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፻፴፪ና ፡ ፻፴፫ ፡ ይህንኑ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቃል ፡ "ፎልት/ጥፋት ፡" ብለውታል ። በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተመረጠው ፡ ትርጉም ፡ "ፎልት/ጥፋት ፡" የሚለው ፡ ነው ።
42. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፫ ።
43. የፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ ፴፰/፩ ።

የተመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የማይገባው ፡ ውድድር ፡ መግለጫ ፡ የአጥፊው ፡ አድራጐት ፡ “ለቅን ፡ ልቡና ፡ ተቃራኒ ፡” መሆን ፡ አለበት ፡ ይላል ።[44] ይህም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፫ን ፡ ይደግመው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፤ ቢሆንም ፡ የኋለኛው ፡ (፻፴፫) የራሱ ፡ መግለጫ ፡ (ማብራሪያ) ፡ ያለው ፡ ስለሆነ ፡ የሚጠይቃቸው ፡ ሁሉ ፡ ከተሟላ ፡ ይህንን ፡ ቁጥር ፡ መጣስ ፡ ልክ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፺፯ን ፡ እንደመጣስ ፡ ይቆጠራል ። በፍትሐብሔር ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ አድራጐት ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ለመባል ፡ የሚጠይቃቸውን ፡ ነገሮች ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ጉዳዮችም ፡ ውስጥ ፡ ካላስገባናቸው ፡ በስተቀር ፡ በጠቅላላው ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ እንደሚነሱ ፡ ኃላፊነቶች ፡ ሁሉ ፡ በንዝህላልነት ፡ የሚፈጸሙ ፡ ድርጊቶችም ፡ በንግድ ፡ ጉዳይ ፡ እንደጥፋት ፡ የማይቆጠሩበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ።[45]

የተገቢ ፡ ውድድር ፡ መኖር ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማ ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ በቅን ፡ ልቡናና ፡ ያለ ፡ ንዝህላልነት ፡ ቢሠራም ፡ ምልክቱ ፡ ደንበኞችን ፡ የሚያሳስት ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ከባድ ፡ ችግሮችን ፡ ያስከትላል ። በምልክቱ ፡ መጠቀም ፡ የቀጠለ ፡ እንደሆነ ፡ ደንቦቹ ፡ የተዛቡ ፡ ይሆናሉ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሰውየው ፡ ይቀጣ ፡ ለማለት፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ አይመስልም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካሣ ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ሕጉ ፡ በሚያቀርበው ፡ ሰፊ ፡ አማራጭ ፡ መንገድ ፡ በመጠቀም ፡ ትክክለኛ ፡ ከሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነጋዴው ፡ አሳሳች ፡ የሆነውን ፡ ምልክቱን ፡ ወደፊት ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ አዝዞ ፤ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ስለተጠቀመበት ፡ ግን ፡ ካሣ ፡ እንዳይከፍል ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ እቅዳቸው እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ድርጊቶች ፡ ወደፊት ፡ እንዳይኖሩ ፡ ማስወገድ ፡ ከሆነ ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ ከሚከለክሉ ፡ ደንቦች ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ ነው[46] ። ወይም ፡ ነጋዴው ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ ተጠቅሞበት ፡ ብዙ ፡ ደንበኞችን ፡ ያፈራበት ፡ ስለሆነ፡ በምልክቱ ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ ማድረጉ ፡ ትክክለኛ ፡ ሆኖ ፡ የማይታይ ፡ ከሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባካባቢው ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ምልክቱ ፡ እንዳያሳስት ይሻሻል ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ሊያዝዝ ፡ ይችላል ። እንዲያውም ፡ በጊዜው ፡ ባለማቅረቡ ፡ በዚህ ፡ በኋለኛው ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ በሚቀርብ ፡ ሙግት ፡ ከሳሽ ፡ ክሱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካሣ ፡ ላይወስን ፡ ይችላል ።[47]

የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሚፈጸም ፡ ጥፋት ፡ ዘር ፡ ስለሆነ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፪ — ፻፴፬ ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠቀሱ ፡ በቀሩት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ጥፋት ፡ የሚናገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ አላቸው ። ለምሳሌ ፤ ስለ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፤ ማስረጃ ፡ የትኛው ፡ ወገን ፡ ማቅረብ ፡ እንዳለበት ፤ የኪሳራ ፡ መጠን ፤ ሰዎችና ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ስለሌሎች ፡ ሥራ ፡ ያለባቸው ፡ ኃላፊነትና ፡ ወዘተ

---

44. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ ፡ ፺፯ ፡ “አንድ ፡ ሰው ፡ ሐሰተኛ ፡ በሆነ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ቅን ፡ ልቡናን ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ አድራጎት ፡ የአንዱን ፡ የፋብሪካ ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ (ዕቃ) ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ መልካም ፡ ስም ፡ የሚያጠፋ ፡ ስብከት ፡ ያደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ።
45. ፒ ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፺፬ ፡
46. ከዚያው ፡ ቁጥሮች ፡ ፺፱ ፡ ፻፲፩ን ፡ ይመለከቷል ።
47. የፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፪ሺ፺፯ንና ፡ ፪ሺ፹፩ን ፡ ያወዳድሯል ።

ረፈ ፡ የምናገኘው ፡ ከተጠቀሰው ፡ የፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ነው ።[48] አንዳንድ ፡ ሊወሰኑ ፡ የሚችሉ ፡ መድኀኖችም ፡ በቁጥር ፡ ፻፴፬ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ ተጠቅሰዋል ። የተጐዳው ፡ ሰው ፡ በማይገባ ፡ ከሚወዳደረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ኪሳራ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ለማስወገድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ያዝለታል ፤ ይህም ፡ በተለይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍትሐብሔር ፡ሕግ፡ መጽሐፍ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ በሚል ፡ አንቀጽ ፡ በቁጥር ፡ ፪ሺ፪፰ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ በማይገባ ፡ በተወዳደረው ፡ ነጋዴ ፡ ኪሳራ ፡ አሳሳቹ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ያስከተለውን ፡ ውጤት ፡ ለማጥፋት ፡ በማስታወቂያ ፡ እንዲገለጽና ፡ በዚያው ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፪፭፱ ፡ መሠረት ፡ በማይገባ ፡ የሚወዳደረው ፡ ነጋዴ ፡ ይህን ፡ አሳሳች ፡ የሆነ ፡ ድርጊቱን ፡ ሁሉ ፡ ያቆም ፡ ዘንድ ፡ ማዘዝን ፡ ይጨምራል ። በምልክቱ ፡ እንዳይሠራበት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ በጊዜያዊነት ፡ መልክ ፡ ክሱ፡ እንደቀረበ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊፈቀድ ፡ ይችላል ።[49] እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተጠየቀውን ፡ መድኀን ፡ ከተሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ አገናዝቦ ፡ በመፍቀድ ፡ ረገድ ፡ ብዙ ፡ አማራጭ ፡ መንገድ ፡ አለው ።

በመሠረቱ ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ የሚከለክሉት ፡ ደንቦች ፡ ለአንድ ፡ ነጋዴ ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ የማይሰጡ ፡ መሆናቸውን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ፤ እነዚህ ፡ ሕጐች ፡ ቀድሞ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለውን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ እንዳይቀዳ ፡ ለማድረግ ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ። ኃይለ ፡ ቃሉም፡ በመጀመሪያው ፡ ተጠቃሚ ፡ የባለንብረትነት ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፤ በሁለተኛው ፡ ተጠቃሚ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ድርጊት ፡ ላይ ፡ ነው ።[50] ስለዚህ ፡ ለአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ አማካኝነት ፡ ጥበቃ ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በምልክቱ ፡ ላይ ፡ የባለንብረትነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥያቄ ፡ አይደለም ። ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ለብዙ ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ ምሁራን ፤[51] እንቆቅልሽ ፡ ሆኖ ፡ የቆየ ፡ ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግም ፡ በቀላሉ ፡ መልስ ፡ ያገኘለት ፡ አይደለም ። የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ከንግድ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሀብት ፡ መብትነት ፡ የተመዘገቡና ፡ ሕጉ ፡ እንደሀብት ፡ የሚቆጥረው ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡

48. በጠቅላላው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺን - ፪ሺ፩፻፷፩ ፡ ይመለከቷል ። ከሳሹ ፡ ተከሳሹ ፡ አላግባብ ፡ ያገኘውን ፡ ትርፍ ፡ ማግኘት ፡ ስለሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ አላግባብ ፡ መበልፀግን ፡ የሚመለከቱትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፪ሺ፪፻፷፪ን ፡ ፪ሺ፪፻፷፫ን ፡ ያወዳድሯል ፡ በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በማይገባ ፡ ውድድርና ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ በሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ መፍትሔዎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ ፒ፡ሩብየርን ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ቮል ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ን ፡ ይመለከቷል ። እሱም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዲኖር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በደል ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ መድረሱን ፡ ማሳየት ፡ ቢያስፈልግም ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ፡ ጠንከር ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰው ፡ መሳከርን ፡ የሚያስከትል ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ዕውን ፡ የሆነ ፡ በደል ፡ መድረሱን ፡ በማሳየት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ፡ ዝቅተኛ ፡ እንዲሆን ፡ እንደሚያደርገው ፡ ያስገነዝባል ። ይህም ፡ የማይገባ ፡ ድርጊትን ፡ ለመከላከል ፡ ከተጠነሰሰው ፡ መሠረት ፡ ሃሳብ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው ፡ ከሳሹ ፡ የሚሻው ፡ ኪሣራን ፡ ማግኘት ፡ እንደሆነ ፤ ኪሣራ ፡ የሚሰጥበት ፡ መሠረት ፡ ሀሳብ ፡ በከሳሹ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ጉዳት ፡ የመሸፈኑ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሆነ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳት ፡ (ምንም ፡ እንኳ ፡ የጉዳቱን ፡ መጠን ፡ መመዘኑ ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆን) ፡ መድረሱን ፡ ማሳየት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

49. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፶፫ ።

50. ፒ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥሮች ፡ ፬ ፡ ፻፲፬ ፡ ፻፲፭ ። እሱም ፡ በተለየ ፡ ሕግ ፡ በተጠበቁ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ መብቶችና ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ ድንጋጌዎች ፡ በተከለከሉት ፡ ጥፋቶች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ያብራራል ።

51. ለምሳሌም ፡ ኤፍ ፡ ሼክተር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ይመለከቷል ።

እንደተቋቋመበት ፡ ነገር ፡ ተቆጥረዋል ።[52] በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡[53] በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስለድርሰትና ፡ ስለኪን ፡ ጥበብ ፡ ንብረትንት ፡ ትርጓሜ፡ እንደተሰጠው፡ ዓይነት ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ንብረትነት ፡ በግልጽ ፡ የተደነገገበት ፡ ቦታ ፡ የለም ። ፓርላማ ፡ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ሕግ ፡ እንዲያወጣ ፡ ቢደረግ ፡ በመሠረቱ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አርቃቂ ፡ በቁጥር ፡ ፻፵፰ ፡ ልዩ ፡ ሕጎች ፡ ሲል ፡ የጠቀሰው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[54] መብትን ፡ መነሾ ፡ አድርገን ፡ በማሰብ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ንግድ ፡ ምልክት ፡ የመጠቀም ፡ መብትን ፡ ስለሚያገኝበት ፡ ሁኔታ ፡ ለመመርመር ፡ ብንሻ ፡ (ለዚሀ ፡ ጉዳይ ፡ በቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ መሠረት)[55] መብቱን፡ ለማስከበር ፡ (ለመጠበቅ) ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንዳለበት ፡ ማጥናት ፡ ይኖርብናል ። ተበደልኩ ፡ ባዩ ፡ ጥፋት ፡ ሠርቷል ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ተወዳዳሪ ፡ መሆኑን ፡ ካሳየና ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፮/ሀ ፡ መሠረት ፡ የተገለገለበት ፡ ምልክት ፡ ከዕቃዎቹ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ የምልክቱ ፡ በአጥፊው ፡ መቀዳት ፡ ደንበኞችን፡ እስከሚደርስበት ፡ ነጥብ ፡ ድረስ ፡ መሆኑን ፡ በማሳየት ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ የሚያዝዘውን ፡ ካሟላ ፡ ይበቃል ። ይህም ፡ ከፍ ፡ ብለን ፡ ወደ ፡ ተነጋገርንባቸው ፡ ትርጓሜዎች ፡ ይመልሰናል ። በተጨማሪም ፡ ከሳሽ ፡ ምልክቱን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችል፡ ዘንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ከሌሎች ፡ ሳይመሳሰል ፡ በቂ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማስረዳት ፡ ይኸው ፡ ምልክት ፡ ሊጠበቅለት ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ማሳየት ፡ ይኖርበታል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ በመጀመሪያ ፡ ምልክቱ ፡ ለሚሠራው ፡ ዕቃ ፡ እንደመግለጫ ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራበት ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ ከሳሽ ፡ ከሚሠራው ፡ ዕቃ ፡ ጋር ፡ የሚያስተሳስር ፡ ስሜትን ፡ በደንበኞች ፡ ላይ ፡ አሳድሯል ፡ በማለት ፡ በሚነሳው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የተለየ ፡ ችግር ፡ ይፈጥራል ።[56] ምዝገባ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንነጋገርበታለን ።

፮/ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፬ ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፬ ፡ በወንጀል፡ ስለሚያስቀጣ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ይናገራል ። ይህም ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ አስመስሎ ፡ በሚሠራበት፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ ሊኖረው ፡ ይችል ፡ ይሆናል ፤ ሆኖም ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፬ ፡ በይበልጥ ፡ ቀጥተኛ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከት ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ የምንነጋገርበት ፡ አርእስት ፡ ይሆናል ።

ቁጥር ፡ ፮፻፴፬ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

(፩) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡—

(ሀ) ሕዝብን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ለመምራት ፡ ሲል ፡ በንግዱ ፡ እቃም ፡ ሆነ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የፋብሪካ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ በእንዱስትሪና ፡ በእርሻ ፡ መኪናዎችና ፡ እቃ

---

52. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፯፻፷፯ ፡ ፯፻፷፰ ። ስለነዚሀ ፡ ቁጥሮች ፡ ትርጓሜ ፡ ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ን ፡ ይመለከቷል ።
53. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፵፰ ።
54. በፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደሆነው ፡ ሁሉ ፡ ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፵፫ን ፡ ይመለከቷል ።
55. በሌሎች ፡ ቁጥሮች ፡ ሥር ፡ የተደረገው ፡ ጥበቃ ፡ በእነዚያው ፡ ቁጥሮች ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ እንደሚሆን ፡ እያጠራጥርም ፡ ለምሳሌም ፡ ከዚሀ ፡ በታች ፡ የተገለጸውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፬ን ፡ ይመለከቷል ።
56. ኢ ፡ አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፹፮ ፡ ይመለከቷል ።

ዎች ፡ ላይ ፡ የተሠሩበትን ፡ የመጡበትን ፡ አገር ፡ ዓይነታቸውንና ፡ ማርካቸውን ፡ ለመ ለየት ፡ በላያቸው ፡ የተለጠፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመጠቅለያቸውና ፡ በሳጥናቸው ፡ ላይ ፡ የተደረጉትን ፡ ምልክቶች ፡ የለወጠ ፡ ያስመሰለ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የራሱ ፡ ያደ ረገ ፡ እንደሆነ ፤ . . . የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብበት ፡ በእሥራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።

እንዲሁም ፤ በማስመሰል ፡ የተሠሩ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የተደረጉ ፡ የንግድ ፡ ምል ክቶች ፤ እንዳላቸው ፡ እያወቁ ፡ የንግድ ፡ እቃዎችን ፡ የሸጡ ፤ ለሽያጭ ፡ ያቀረቡ ፡ ወደ፡ ውጭ ፡ የላኩ ፤ ወይም ፡ ከውጭ ፤ አስመጥተው ፡ ባገር ፡ ወስጥ ፡ ያስገቡ ፤ ያደሉ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ እጅ ፡ እንዲዘዋወሩ ፡ ባደረጉ ፡ ሰዎችና ፡ በእጃቸው ፡ የሚገኙትን ፡ የንግድ ፡ እቃዎች ፡ ከወዴት ፡ እንደመጡ ፡ ለመግለጽ ፡ እንቢተኛ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፤ ተመሳሳይ ፡ ቅጣት ፡ ተወስኗል ።[57]

ይህ ፡ ቁጥር ፡ አጥፊው ፡ ገዥውን ፡ ሕዝብ ፡ ለማሳሳት ፡ በፈጸመው ፡ የማይገባ ፡ ድርጊት ፡ ላይ ፡ ያተኰረ ፡ ስለሆነ ፤ በመሠረቱ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ የአንቀጹ ፡ አግባብነት ፡ ከንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ የሠፋም ፡ የጠበበም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፸፭ን ተላልፎ ፡ መገኘት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፶፯ ፡ መሠረት ፡ በተጨማሪ ፡ የጉዳት ፡ ካሣን ፡ የሚያስጠይቅ ፡ ስለ ሆነ ፤ በወንጀል ፡ በኩል ፡ መፍትሔ ፡ ለማይፈልገውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፤ ልዩነቶቹ ፡ አስፈላጊ ፡ ናቸው ።

አስመስሎ ፡ የመሥራቱ ፤ ገዥዎችን ፡ የማሳሳቱና ፡ የንግድ ፡ እቃዎችን ፡ የሚመ ለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ እስከ ፡ ተጠቀሱ ፡ ድረስ ፤ በቁጥር ፡ ፮፻፸፬ና ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፮፻፸፮ ፡ በሐሰት ፡ የራስ ፡ ስለማድረግ ፤ ስለማስመሰልና ፡ ስለመለወጥ ፡ ይናገራል ፤ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ትርጉም ፡ ተሰጥቷቸዋል ።[58] ቁጥር ፡ ፮፻፸፮ ፡ “ተወዳዳሪውን ፡ ለማሳከር ፡ ሲባል ፤” በማለት ፡ ፋንታ ፡ “ሕዝብን ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ (ስለ) መምራት” ፡ ይላል ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ሐረጐች ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ሊተረጐሙ ፡ ይገባል ።[59] ምናልባት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ ሐረግ ፡ እር

---

57. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፸፮ (ለ)ና ፡ (ሐ) ፡

58. “ወደ ፡ ሐሰት ፡ የለወጠ”ና ፡ “ያስመሰለ/ያስተላለፈ ፡” ፡ የሚባሉት ፡ ቃላት ፡ በመጠኑም ፡ ቢሆን ፡ የተለ ያየ ፡ ትርጉም ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ። ለምሳሌም ፡ በእንግሊዝ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ “ወደ ፡ ሐሰት ፡ መለ ወጥ ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ በንግድ ፡ ምልክት ፡ ምዝገባ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተመዘገበን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ማስመሰል ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። ሐልስበሪ ፡ ሎውስ ፡ ኦፍ ፡ ኢንግላንድ ፡ (ሦስተኛ ፡ እትም ፡ ሎንደን ፡ በተርዎርዝ ፡ ፲፱፻፶፱ ) ፴፩ ፡ ፴፰ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ የንግድ ፡ ስሞችና ፡ ስዕሎች ፡ ገጽ ፡ ፯፻፷፰ ። የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ቅጅ ፡ የተጠቀመበት ፡ “ኮንትርፌ” ፡ የሚለው፡ ቃል ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ትርጉሙ ፡ “ወደሐሰት ፡ መለወጥ/ ፡ ኢንፍሪንጅመንት ፡” የሚለው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ትርጉም ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ፡ ምናልባት ፡ የሕጉ ፡ አርቃቂዎች ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፸፮ ፡ የተለየ ፡ የምዝገባ ፡ ሕግ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የተመዘገበ ፡ ምልክትን ፡ በማስመሰል ፡ ለሚፈጠረው ፡ ሁኔታ ፡ መድኀን ፡ ይሆናል ፤ በተጨማሪም ፡ ያልተመዘገቡ ፡ ምልክቶችንም ፡ መመሳሰል ፡ የሚመለከት ፡ ጠቅላላ ፡ መድኀን ፡ ይሰጣል ፡ ብለው ፡ አስበው ፡ ይሆናል ። “ማስመሰል/ ማስተላለፍ ፡” ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ በእንግሊዝ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ንግድ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ የሚደረገውን ፡ የሐሰት ፡ ውክልና ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። ሃልስበሪ ፡ ሎውስ ፡ ፴፩ ፡ ፴፰ ፡ ገጾች ፡ ፯፻፺፫-፯፻፺፮ ። ስለዚህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ የማይገባ ፡ ውድ ድር ፡ ጽንሰ ፡ ሀሳብ ፡ ጋር ፡ በመሠረቱ ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ።

59. በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ የሚገኘው ፡ የዚህ ፡ ሐረግ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቅጅ ፡ በቁጥር ፡ ፮፻፸፮ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ሐረግ ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ነው ፡ ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፩ንና ፡ አብሮት ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ይመለከቷል ።

ግጠኛ ፡ የሆነ ፡ መሳከርን ፡ ይጠይቃል ፡ የሚል ፡ ሙግት ፡ ይቀርብ ፡ ይሆናል ፤ ስለሆነም ፡ እርግጠኛ ፡ የሆነ ፡ መሳሳትን ፡ በአስረጅ ፡ በመደገፍ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ችግርና ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፸፱ ፡ ከማይገባ ፡ ውድድር ፡ ጋር ፡ ባለው ፡ ጠቅላላ ፡ ግንኙነት ፡ አንጻር ፡ እስከተመለከትነው ፡ ድረስ ፤ ይህን ፡ መሰሉ ፡ ቀጥተኛ ፡ ትርጉም ፡ ተሰሚነት ፡ አይኖረውም ፡ (ከዚህ ፡ በታች ፡ ተዘርዝሮ ፡ ያለው) ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የማድረግ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ መሟላት ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ የአጥፊውን ፡ ጥቅም ፡ ስለሚጠብቀውና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የወንጀል ፡ ቅጣቶች ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ መቀጫዎች ፡ ጠንከር ፡ ብለው ፡ ስለሚገኙ ፤ ጥብቅ ፡ የሆነ ፡ የአንቀጹ ፡ አተረጓጎም ፡ የማይደገፍ ፡ ይሆናል ። "ደንበኛ ፡" በማለት ፡ ፈንታም ፡ "ሕዝብ ፡" የሚለው ፡ ቃል ፡ መተካቱም ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፸፱ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ ውድድር ፡ በቀደምት ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ አለመሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ የታቀደ ፡ ነው ።

በቁጥር ፡ ፲፻፸፱ና ፡ በቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ ዋና ፡ ልዩነቶች ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፸፱ ፡ አጥፊውና ፡ ተበዳዩ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ባይሆኑም ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆኑና ፤ አጥፊው ፡ የተጎዳውን ፡ ምልክት ፡ ያስመሰለው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሕዝብን ፡ ለማሳሳት ፡ በሚያስችል ፡ አኳኋን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚ ፡ አለመሆኑ ፡ ነው ።

ቁጥር ፡ ፲፻፸፱ ፡ ውድድርንም ፡ ሆነ ፡ ተወዳዳሪዎችን ፡ አይጠቅስም ፡ ስለዚህም ፡ የአጥፊውና ፡ የተጎጂውን ፡ ወገን ፡ ደንበኞች ፡ አንድ ፡ የመሆናቸው ፡ ጉዳይ ፡ ማለትም ፡ በአንድ ፡ አካባቢ ፤ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ የንግድ ፡ እቃዎችን ፡ መሸጣቸው ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ሆኖም ፡ እነዚህ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ በጠቅላላው ፡ አልተወገዱም ። ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፤ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ በሚመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፤ በንግድ ፡ እቃዎቹ ፡ መካከል ፡ ተመሳሳይነት ፡ ወይም ፡ ግንኙነት ፡ እስከሌለ ፡ ድረስ ፡ መሳከር ፡ ይፈጠራል ፡ ብሎ ፡ ለማለት ፡ የማይቻል ፡ ይሆናል ። ዳግም ፡ እቃዎቹ ፡ በአንድ ፡ አካባቢ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ካልተሸጡ ፡ የመሳከሩ ፡ ሁኔታ ፡ የመነመነ ፡ ይሆናል ። ስለሆነም ፤ ከዚህ ፡ ጋር ፡ የማይገጥም ፡ አንድ ፡ የተጠበቀ ፡ ሁኔታን ፡ መጥቀስ ፡ ይገባል ። አንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ እቃው ፡ በዚያ ፡ አካባቢ ፡ ባይሸጥ ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ አካባቢ ፡ የታወቀ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ለምሳሌ ፤ በማስታወቂያ ፤ በእቃው ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንደገና ፡ ባለመሸጥ ፤ ወይም ፡ የአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከዚያ ፡ አካባቢ ፡ እቃው ፡ ወደሚሸጥበት ፡ አካባቢ ፡ መጓዝ ፡ ነው ። በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ የታወቀውን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ከማስመሰል ፡ የሚመነጭ ፡ መሳከር ፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ።[60] ይህ ፡ ችግር ፡ በተለይ ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ንግድ ፡ ውስጥ ፡ ዐቢይ ፡ ሆኖ ፡ ቆይቷል ። የንግድ ፡ ምልክት ፡ መብቶች ፡ በጠቅላላው ፡ በግዛት ፡ ክልል ፡ የተወሰኑ ፡ ሆነው ፡ የሚገመቱ ፡ ናቸው ። የዚህን ፡ መሰል ፡ መብት ፡ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ መገኘት ፤ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ ከሌለ ፤ በሌላ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ባለመብት ፡ አያደርግም ። ይህም ፡ አስተሳሰብ ፡ በታወቁ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለው ፡ አደገኛ ፡ ሁኔታ ፤ አባሎቹ ፡ በሙሉ ፡ የታወቁ ፡ ምልክቶችን ፡ እንዲጠብቁ ፡ በሚያስገድደው ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ለመጠበቅ ፡

---

60. የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ከፍትሐብሔር ፡ ማስገደጃ ፡ ይበልጥ ፡ የጠነከረ ፡ ሲሆን ፡ ውድድርን ፡ በሚመለከተው ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ድንጋጌ ፡ ከፍትሐብሔሩ ፡ ቁጥር ፡ ላላ ፡ ያለ ፡ መሆኑ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሳይመስል ፡ አይቀርም ። ሆኖም ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ መሳከርን ፡ ያስከትላል ፡ የሚያሰኝ ፡ ሁኔታ ፡ ተፈጥሮ ፡ መገኘት ፡ ስላለበት ፡ ልዩነቱ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ሲመለከቱት ፡ ያለውን ፡ ያህል ፡ አይሆንም ፡ የቀረውንም ፡ ልዩነት ፡ አጥፊው ፡ 'አውቆ ፡ ማጥፋት" ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ በአጥጋቢ ፡ ሁኔታ ፡ ሊመዝነው ፡ ይችላል ።

ፓሪስ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ስምምነት ፡ በሚገባ ፡ ታውቋል ።[61] የታወቁ ፡ ምልክቶች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ በ፯፻፸፬ ፡ መሠረት ፡ ሊጠበቁ ፡ ይችላሉ ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻላል ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ ግን ፡ የተከራካሪዎቹን ፡ ወገኖች ፡ በውድድር ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ የሚጠይቅ ፡ ስለሆነ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጥበቃ ፡ ሊሰጥበት ፡ አይቻልም ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፸፬ን ፡ ከመጣሱ ፡ በፊት ፡ ሊኖረው ፡ የሚገባው ፡ የአእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ በግልጽ ፡ ተነግሯል ። ይኸውም ፡ የሌላውን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ያስመሰለው ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ሕዝብን ፡ ወደሐሰት ፡ ለመምራት ፡ መሆን ፡ አለበት ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ መሠረት ፤ ይህ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፤ አጥፊው ፡ ድርጊቱን ፡ የፈጸመው ፡ ምልክቱ ፡ የሌላ ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ወደሐሰት ፡ ለመምራት ፡ ሲል ፡ የሆነ ፡ ከሆነ ፤ ወይም ፡ ምልክቱ ፡ ሕዝብን ፡ ወደሐሰት ፡ ለመምራት የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ የሆነው ፡ ይሁን ፡ በማለት ፡ ያደረገው ፡ ከሆነ ፡ ተፈጻሚነቱ ፡ የተሟላ ፡ ይሆናል ።

ቁጥር ፡ ፯፻፸፬ን ፡ በጣሰ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚመጡት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ሊመሠረቱ ፡ የሚችሉት ፡ ተጐጂው ፡ ወገን ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ያቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ነው። አጥፊው ፡ በእሥራት ፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ወይም ፡ በሁለቱም ፡ ሊቀጣ ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ በላይ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ የተለወጡትን ፡ እቃዎች ፤ ከእነዚህ ፡ መሰል ፡ እቃዎች ፡ የተገኘውን ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋና ፡ ወንጀለኛው ፡ የተቀበለው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ እንዲወረስ ፡ ይፈርዳል ። በተጨማሪም ፡ ፍርዱ ፡ በጥፋተኛው ፡ ሰው ፡ ኪሣራ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲገለጽ ፡ ይደረጋል ።[62]

ቁጥር ፡ ፯፻፸፬ን ፡ የጣሰ ፡ ሰው ፡ የወንጀልም ፡ የፍትሐብሔርም ፡ ኃላፊነት ፡ ይኖርበታል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፤ "አንድ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ላይ ፡ በትክክል ፡ ተገልጾ ፡ የተመለከተውን ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌ ፡ የጣሰ ፡ እንደሆነ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ፡" በሚለው ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፴፰ ፡ መሠረት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።[63] በቁጥር ፡ ፪ሺ፴፰ ፡ ሥር ፡ የተሰጡት ፡ መፍትሔዎች ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፫ ፡ ሥር ፡ ከተሰጡት ፡ ጋር ፡ በመሠረቱ ፡ የተመሳሰሉ ፡ ናቸው ፤ እነዚህም ፡ ኪሣራ ፤ የማገጃ ፡ ትእዛዝ ፡ ፍርዱን ፡ በአጥፊው ፡ ኪሣራ ፡ ማሳወጅና ፡ "የሰዎች ፡ ነፃነትና ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መብቶች ፡ እንደተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ለጉዳቱ ፡ ኪሣራ ፡ መወሰን ፤ ወይም ፡ ለጉዳቱ ፡ ወሰን ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ "(ማድረግ ፤)" ናቸው ።[64]

---

61. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሀብትን ፡ ለመጠበቅ ፡ የተደረገው ፡ የፓሪሱ ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፮ለ ። ደግሞ ፡ ሉ ፡ አፍ ፡ ዲሲምበር ፡ ፴፩ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ (ፈረንሣይ) ፡ ቁጥር ፡ ፬ ፡ በ "ቅድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡" ፡ (ፔቲ ፡ ኮድ ፡ ደሎዝ ፡ ፷፫ኛው ፡ እትም ፡ ፲፱፻፶፱) ፡ ውስጥ ፡ በገጽ ፡ ፯፻፷ ፡ ይመለከቷል ፡ እ ፡ ሻቫኝ ፡" ላ ፡ ኖሲዮ ፡ ዲ ፡ ፕሪሚየር ፡ ዩዛዥ ፡ ደ ፡ ማርክ ፡ ኤ ፡ ለ ፡ ኮሜርስ ፡ ኢንተርናሲዮኔል ፡ "በ ፡" ሜላንዥ ፡ ኧን ፡ ለ ፡ ኦነር ፡ ደ ፡ ፖል ፡ ሩብየር ፡ "(ፓሪስ ፡ ሊብ ፡ ዳሎዝና ፡ ሲሬይ ፡ ፲፱፻፷፩) ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፷፻፳፫ ።

62. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፹፱ ፡ ፺፱ ፡ ፯፻፲፯ ፡ ፯፻፸፬ ፡ ፯፻፸፮ ፡ ፯፻፹፯ ። በአንዳንድ ፡ በተለዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ሊሠሩባቸው ፡ ስለሚችሉ ፡ ተጨማሪ ፡ ቅጣቶች ፡ ሊደረጉ ፡ ስለሚችሉ ፡ የጥንቃቄና ፡ የጥበቃ ፡ እርምጃዎች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የ፻፳-፻፳፯ ፡ ፻፴፰-፻፵፫ ፡ ይመለከቷል ።

63. ከወንጀል ፡ ክሶች ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ስላለው ፡ ኪሣራ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፺ን ፡ በተጨማሪ ፡ ይመለከቷል ፡ ስለጠምራ ፡ ክስ ፡ ፒ ፡ ግራቨን ፡ "የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጠምራ ፡ ክሶች ፡" የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪(፲፱፻፷፭) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፩ ፡ ይመለከቷል ።

64. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፪ሺ፴፯ ፡ ፪ሺ፻፳-፪ሺ፻፳፬ (ከቁጥር ፡ ፪ሺ፴፯/፪ ፡ እንደተጠቀሰ) ።

## ፫/ ስለንግድ ፡ ምልክቶች ፡ አመዘጋገብ ፤

በማይገባ ፡ ውድድር ፡ ዘዴ ፡ መሠረት ፡ (በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፸፬ ፡ የተሰጠውን ፡ የመሰለ ፡ መፍትሔ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡) የሚደረገው ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ጥበቃ ፤ በንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ከባድ ፡ ችግሮችን ፡ ይፈጥራሉ ። እነዚህንም ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ምዝገባን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሕጎች ፡ አውጥተዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ በሚያስከትሏቸው ፡ ውጤቶች ፡ የተለያዩ ፡ ቢሆኑም ፤ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ነጋዴዎች፡የሌሎች፡የሆኑትን ፡ ምልክቶች ፤ እንዲያውቁና ፡ የራሳቸውንም ፡ ምልክቶች፡ሌሎች ፡ እንዲያውቁላቸው ፡ ያደርጋሉ ። አንድ ፡ የምዝገባ ፡ ሕግ ፡ ሬጅስትራሩ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውን ፡ (ፈራሽ ፡ የሆኑትን) ፡ ምልክቶች ፡ እንዳይቀበላቸው ፡ በማድረግ ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ምልክቱ ፡ ሕጋዊ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ በቅድሚያ ፡ እንዲያረጋግጥ ፡ ይረዳዋል ፡ ምዝገባ ፡ የአንድን ፡ ምልክት ፡ ሕጋዊነት ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንድ ፡ የንግድ ምልክት ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላም ፡ በጠቅላላ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ እንዲሰራበት ፡ መደረጉ ስለሆነ ፡ ነጋዴው ዕቃውን በማይሸጥባቸው ፡ ገበያዎችም ፡ ውስጥ ፡ ጥበቃ ፡ እንደሚደረግለት ፡ ማረጋገጫ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንዳንድ ፡ ሕጎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ምልክታቸውን ፡ ለጊዜው ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ከሚያውሉባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ሌላ ፡ በሌሎች ፡ ዕቃዎችም ፡ ላይ ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ በመስጠት ፡ ምልክታቸው ፡ ተውጦ ፡ ከመቅረት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ያደርጋሉ ። ሌሎች ሕጎች ፡ ደግሞ ፡ ነጋዴው ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ካሰበው ፡ ምልክቱ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ ምልክቶችን ፡ እንዲያስመዘግብ ፡ በመፍቀድ ፡ የምልክቱ ፡ ልዩነት ፡ እንዲተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የጥበቃው ፡ መጠን ፡ እንዲሰፋ ፡ ያደርጋሉ ። አንዳንዶችም ፡ ነጋዴው ፡ ወደፊት ፡ ሊጠቀምበት ፡ ያሰበውን ፡ ምልክት ፡ በማስመዝገብ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ይፈቅዳሉ ። ምዝገባ ፡ ነጋዴው ፡ በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ ምልክቱን ፡ አስመዝግቦ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ በውጭ ፡ ሀገሮችም ፡ ምልክቱ ፡ ሊጠበቅለት ፡ ይችላል ፡ በሚሉ ፡ ስምምነቶችና ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕጎች ፡ እንዲጠቀም ፡ ይረዳዋል ። በመጨረሻም ፡ የምዝገባ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ማስተላለፍንና ፡ ፈቃድ ፡ መስጠትን ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ሐሰት ፡ ስለመለወጥ ፡ ልዩ ፡ መፍትሔዎችንና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ አጠቃላይ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕጎች ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ናቸው ።[65]

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለሚኒስትሮች ፡ (ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ አወሳሰን ፡ በወጣ ፡ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፩/መ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡

---

65. ኢ ፡ አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ አ ፡ ሻሻኝ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሞዴል ፡ ሕግ ፡ (የተሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ ጨምሮ) ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ በተለይም ፡ በ፲፱፻፺፰ ፡ የዩናይትድ ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ቢሮ ፡ ስለድርሰትና ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ባለሀብትነት ፡ ጥበቃ ፡ ሳልበሰጹት ፡ አገሮች ፡ ያዘጋጀው ፡ የምልክቶች ፡ የንግድ ፡ ስሞች ፡ (ዕቃዎች) ፡የመጠብትን ፡ አገር ፡ ማመልከቻዎችና ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ሞዴል ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ (ኢ ፡ አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ አስተያየት ፡ እንደሰጠበት) ፡ እና ፡ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአፍሪካና ፡ የማልጋሲ ፡ ስምምነት ፡ ፈራሚ ፡ ሀገሮች ፡ የተቀበሉትን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕግ ፡ ይገነዘቧል ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕጎች ፡ የተደረገ ፡ ጥናት ፡ በናሽናል ፡ አሶስዬሽን ፡ አቭ ፡ ክሬዲት ፡ ማኔጅመንት ፣ ዳይጀስት ፡ አፍ ፡ ኮሜርሺያል ፡ ሎስ ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ወርልድ ፡ (ዮብስ ፡ ፌሪ ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ አሺያና ፡ ፐብሊኬሽንስ ፡ ሉዝ ፡ ሊፍ ፡) ስለ ፡ እንዱስትሪ ፡ ባለሀብትነት ፡ ስለንግድ ፡ ምልክቶች ፡ በተለይ ፡ በወጣ ፡ ቮልዩም ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። አንዳንድ ፡ ብሔራዊ ፡ የሆኑ ፡ የምዝገባ ፡ ሕጎች ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስታወሻዎች ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሰው ፡ ይገኛሉ ፡ ለምሳሌም ፡ ፈረንሳይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ ኢንግላንድ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ካናዳ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፯ ። ዳግም ፡ ዊብስተር ፡ "ፓተንትስ ፡ ትሬድ ፡ ማርክስ ፡ ኤንድ ፡ ዲዛይንስ ፡ ኢን ፡ አፍሪካ ፡ ፕሪቶሪያ ፡ ፓትሎው ፡ ፲፱፻፺፫) ፡ ይመለከቷል ።

መዝገብ፤ እንዲያዘጋጅ ፡ ታዟል ።[66] ስለሆነም ፡ አንድን ፡ ነጋዴ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ እንዲያስመዘግብ ፡ የሚያዝ ፡ ወይም ፡ ምዝገባ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ የሚገልጽ ፡ ሕግ ፡ የለም ።

የንግድ ፡ ስሞች ፡ መሠረት ፡ በሚቀርቡ ፡ የምዝገባ ፡ መግለጫዎች ፡ ውስጥ ፡ መጠቀስ ፡ ይኖርባቸዋል ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህም ፡ ቢሆን ፡ የሚያስከትለው ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ ስላልተገለፀ ፡ ለመረጃ ፡ ያህል ፡ የሚሰጥ ፡ መስሎ ፡ የሚታይ ፡ ነው ።[67] እዋጁም ፡ ስለንግድ ፡ ምልክቶች ፡ አይናገርም ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩፻፮(ቀ)፩፻፩(በ)ና ፡ ፩፻፺(መ) የንግዱን ፡ ስምና ፡ የሚነገድበትን ፡ የተለየ ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስሌዳ፣ በዋናው ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ መግለጽ ፡ እንዳለባቸው ፡ ቢናገሩም ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ አይጠቅሱም ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ ይሀ ፡ እነዚሀ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ገና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋሉም ።[68]

የንግድ ፡ ምልክት ፡ ምዝገባ ፡ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ የሚናገር ፡ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ ምናልባት ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤትን ፡ አያስከትሉም ፡ ማለት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ቢሆንም ፡ ምዝገባ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ አለ ። ስሌሎች ፡ ማስታወቂያ ፡ መስ ጠት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ብልሀ ፡ የሆነ ፡ ነጋዴ ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ ከማስመዝ ገቡ ፡ በፊት ፡ ዋናውን ፡ መዝገብ ፡ ይመረምራል ።

ምዝገባ ፡ በወንጀል ፡ በሚያስጠይቅ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ፡ በተለይም ፡ ወደሐሰት ፡ የለወጠውን ፡ ሰው ፡ የአእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ አግባብ ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ በቀላሉ ፡ ሊተረጎም ፡ ይችላል ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ በዋናው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግበው ፡ ያሉትን ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ሊያውቃቸው ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። መጥፎ ፡ ሕሊና ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ከተቆጠረ ፡ ነጋዴው ፡ የተመዘገቡትን ፡ ምልክቶች ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ በመገመት ፡ ይኸንኑ ፡ ግምት ፡ እንደ ፡ አጠቃላይ ፡ ማስረጃ ፡ ያም ፡ ባይ ሆን ፡ አለማወቁን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ነጋዴው ፡ እራሱ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ይደረጋል ።[69] የንግድ ፡ ሕጉ ፡ የተመዘገቡ ፡ የንግድ ፡ ስሞችንና ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳዎችን ፡ በሚመለከተው ፡ ረገድ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ አጠቃላይ ፡ ግምት ፡ እንዲ ኖር ፡ አድርጓል ፡ ዋናውን ፡ መዝገብ ፡ አለመመርመር ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ የነጋዴውን ፡ ቸልተኝነት ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

---

66. ፲፱፻፶፮ ፡ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ። ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ መ ፡ በሚኒስትሮች ፡ (ሥልጣን ፡ መወሰኛ) ፡ ትዕዛዝ ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ቁጥር ፡ ፴፪ (ሸ) ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመውን ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ መዝገብ ፡ የማቆየቱ ፡ ግዴታ ፡ እንዲቀጥል ፡ አድርጓል ። ቁጥር ፡ ፴፪(ሸ) ፡ በትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ ተሽሯል ።

67. ቁጥሮች ፡ ፪(፩) ለ፩ ፡ ፫(፩)ሐ(፩) ፡ ፬(፩)ሀ(፱) ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፹፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፫ ።

68. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፺ ፡ ፻፸፱/፩ን ፡ ይመለከቷል ።

69. ቁጥር ፡ ፻፷/፪ ፡ "ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ በትክክል ፡ የገባውን ፡ ጉዳይ ፡ አላወቅንም ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አይፈቀድላቸውም" ፡ ይላል ። ስለሆነም ፡ የንግድ ፡ ስሞችና ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በቁጥር ፡ ፻፷፩ ፡ መሠረት ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ እስካልገቡ ፡ ድረስ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የሚገኙን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡" ካልሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ አለመዘርዘራቸውን ፡ መገንዘብ ፡ ይገባል ። በተጨማሪም ፡ እንዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ በቁጥር ፡ ፩፺ ፡ ፻፸፱/፩ ፡ መሠረት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ካልዋሉት ፡ የምዝገባ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መካከል ፡ መሆናቸውን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ።

ምዝገባ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ተመልክተውታል ። በቅርቡ ፡ የጠ.ን.ነ. ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንደኛው ፡ ምልክት ፡ ከሌላው ፡ በፊት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ተመዝጋቢው ፡ ሁለተኛው ፡ ብቻ ፡ የሆነበትን ፡ የሁለት ፡ ምልክቶችን ፡ ግንኙነት ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ሰምቷል ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ አቶ ፡ አዛነው ፡ ዓለሜን ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፻፴፫ ፡ መሠረት ፡ ሲንጀር ፡ ከሚጠቀም በት ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ የመለያ ፡ ምልክት ፡ እንዳይጠቀሙ ፡ ለማገድ ፡ ከሷቸው ፡ ነበር ።[70] ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ምልክቱን ፡ የተጠቀሙበት ፡ ከስፌት ፡ መኪናዎች ፡ ጋር ፡ በተያያዘ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ነው ። የሲንጀር ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ (የሥራ ፡ ውጤቶችና) ፡ የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ከአቶ ፡ አዛናው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በብዙ ዓመታት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ከመዋላቸው ፡ በላይ ፡ ሲንጀርም ፡ ከአቶ ፡ አዛናው ፡ ሠላሳ ፡ ዓመታት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ አውጥቷል ። ቢሆንም ፡ አቶ ፡ አዛናው ፡ የንግድ ፡ ምልክታቸውን ፡ በንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲያስመዘግቡ ፡ ሲንጀር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አላደረገም። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሲንጀር ፡ በመፍረድ ፡ አቶ ፡ አዛናው ፡ በምልክቱ ፡ እንዳይጠቀሙ ፡ ከለከላቸው ፡[71] የጠ.ን.ነ.ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ከአንደኛው ፡ ዳኛ ፡ በስ ተቀር ፡ ፍርዱን ፡ ሲሽር ፡ የሚከተለውን ፡ አትቷል ፡ ጉዳዩን ፡ ከንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ምዝገባ ፡ ወይም ፡ ከብቸኛ ፡ ባለሀብትነት ፡ ሕግ ፡ (የዚሀ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ በኢት ዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለሌለ) ፡ አንጻር ፡ መመልከት ፡ አይቻልም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ከአንድ ፡ ውሳኔ ፡ መድረስ ፡ እንችል ፡ ዘንድ ፡ ፍትሃን ፡ መመርኰዝ ፡ ስላለብን ፡ በታወቁት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ባለው ፡ ዋና ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ "S" (ኤስ) የሚለውን ፡ ፊደል ፡ በመጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ምልክት ፡ ያስመ ዘገቡ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ መለየት ፡ ይኖርብናል ። በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በይበልጥ ፡ ትክክለኛ ፡ ለመሆን ፡ ፍትሃን ፡ ለመከተል ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ የአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ብቸኛ ፡ ባለመብት ፡ በመሆን ፡ ሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ እንዳይጠቀሙበት ፡ ለመከላከል ፡ የሚችለው ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ ለመመዝገብ ፡ ሥልጣን ፡ ባላቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ ለማስመዝገብ ፡ የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ በመሆን ፡ የንግድ ፡ ምልክ ቱን ፡ በማስመዝገብ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ እንዲውል ፡ ካላደረገ ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ተጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ የምልክቱ ፡ ብቸኛ ፡ ባለመብት ፡ ሊሆንና ፡ ሌሎች ፡ እንዳይጠቀሙ ፡ ሊከለክል ፡ አይችልም ። የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ የሚመለከት ፡ ሕግ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ፍትሃና ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከቱ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕጎች ፡ መንፈስ ፡ እንዲሁም ፡ በውጭው ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ልምድ ፡ የሁ ለቱን ፡ ወገኖች ፡ መብቶች ፡ ለመለየት ፡ መዝገቦቹን ፡ እንድንመረምር ፡ ያስገድዱናል ።[72] ዳግም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ "ምዝገባ ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡

70. የምልክቶቹ ፡ ሁኔታ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥሮች ፡ ፳፰-፴፩ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጿል ። የተከሳሹ ፡ ምልክት ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስሌዳ ፡ እንጂ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ አለመሆኑን ፡ ይገነዘቧል ፡ የሌላን ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ በማስመሰል ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሰው ፡ ኃላፊነት ፡ ልዩነቱ ፡ ጠቃሚነት ፡ የለውም ፡ ከላይ ፡ ገጽ ፡ ፩ን ፡ ይመለከቷል ።

71. የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያና ፡ የአዛናው ፡ ዓለሜ ፡ ጉዳይ ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺፫ ።

72. የአዛናው ፡ ዓለሜና ፡ የሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያና ፡ የአዛናው ፡ ዓለሜ ፡ ጉዳይ ፡ (፲፱፻፷፪) የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮል ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲፫ ።

የሚከናወን ፡" መሆኑን ፡ ገልጿል ።[73] ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ ራሱን ፡ እን ደቻለ ፡ ባሕሪ ፡ ሀሳብ ፡ በመቁጠር ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ምልክቶች ፡ መሳከርን ፡ ሊያስከትል ፡ በሚያስችል ፡ አኳኋን ፡ የማይመሳሰሉ ፡ ናቸው ፡ በሚል ፡ እምነት ፡ ባሕሪ ፡ ሀሳቡ ፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ፡ በማለት ፡ ሳይቀ በለው ፡ ቀርቷል ።[74] የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፫፬ ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ ፍ/ቤትም ፡ ሆነ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያልተጠቀሰ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የክስ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ አልቀረበም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በንግድ ፡ ምልክቶች ፡ ለመጠቀም ፡ መኖር ፡ የሚገባው ፡ ሰላምና ፡ የተረጋጋ ፡ ሁኔታ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ በሚገባ ፡ እንዲጠበቁ ፡ ሲፈለግ ፡ መመዝገብ ፡ ይኖርባ ቸዋል ፡ የሚለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ፡ የሚደገፍ ፡ ያደርገዋል ። ዋናውን ፡ መዝገብ ፡ በመመርመር ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ሊጠቀምበት ፡ ያሰበው ፡ ምልክት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ መቻሉንና ፡ አለመቻሉን ፡ ማጣራት ፡ ይችላል ። ምልክቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተመዘገበለትም ፡ ከመመሰልና ፡ በጠቅላላው ፡ ጉዳትን ፡ ከሚያመጡ ፡ ሁኔታዎች ፡ (በተለይም ፡ የምዝገባው ፡ ዘዴ ፡ ምልክቱን ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡) ፡ ሊጠበቅለት ፡ እንደሚችል ፡ ያውቃል ።[75] ነገር ፡ ግን ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ እርግጠኛ ፡ ለመሆን ፡ ያለው ፡ ፍላጐት ፡ በሌሎች ፡ ፍላጐቶች ፡ ተውጦ ፡ ሊቀር ፡ ይችላል ፡ ለምሳሌም ፡ እምነት ፡ የጐደለውን ፡ ጠባይ ፡ ማስቀረት ፡ የደንበኞችን ፡ መታለል ፡ መከላከልና ፡ ለትክክለኛነት ፡ ሲባል ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ (ማለትም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ምልክት ፡ ሳያስመዘግብ ፡ በፊት ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ ሳያስመዘግብ ፡ ሲጠቀምባቸው ፡ የቆየው ፡ ሰው) ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ሊደረግለት ፡ የሚገባ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ በተለይ ፡ ሊፈጠር ፡ የሚችለው አስመዝጋቢው ፡ ሰው ፡ ስለምልክቱ ፡ ወይም ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ ስለሆነው ፡ ሰው ፡ በቂ ፡ ዕውቀት ፡ እያለው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ጥሩ ፡ ስም ፡ ለመጠቀም ፡ ሲል ፡ የራሱን ፡ ምልክት ፡ ባስመዘገበ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አስመዝጋቢው ፡ በምልክቱ ፡ መጠቀሙን ፡ እንዲ ቀጥል ፡ ቢደረግ ፡ ከዕውነት ፡ የራቀን ፡ አድራጐት ፡ ማበረታታት ፡ ይሆናል ፡ የደንበኞ ችንም ፡ መታለል ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በምልክቱ ፡ መጠቀሙን ፡ እንዲያቋርጥ ፡ ማዘዝ ፡ ያተረፈውን ፡ ጥሩ ፡ ስም ፡ ከማጣቱም ፡ በላይ ፡ ይህንኑ ፡ ስሙን ፡ በአዲስ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ላይ ፡ የመገንባት ፡ ኪሣራ ፡ ሊወድቅበት ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለንግድ ፡ ምልክት ፡ እርግጠኛነትን ፡ ለመፍጠር ፡ ሲባል ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ ይሆናል ።

ለንግድ ፡ ምልክት ፡ እርግጠኛ ፡ ሁኔታን ፡ ለመፍጠርና ፡ ምልክታቸውን ፡ ያላስ መዘገቡ ፡ ቀዳሚ ፡ ተጠቃሚዎችን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ በሚወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ችግር ፡ በተለያዩ ፡ አገሮች ፡ የተለያዩ ፡ መፍትሔዎች ፡ ተገኝተው ላቸዋል ። በአንዳንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ምልክቱን ፡ ያላስመዘገበው ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ምልክቱን ፡ ካስመዘገበው ፡ ወገን ፡ ይበልጥ ፡[76]

---

73. ከዚያው ።

74. ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥሮች ፡ ፻፳-፻፳፫ና ፡ ጽሑፋቸውን ፡ ይመለከቷል ፡

75. ኢ ፡ እፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፩፻፴፯ ።

76. ለምሳሌም ፡ ኢ ፡ ባንደንበር ፡ ፫ ፡ ትሬድ ፡ ማርክ ፡ ሎ ፡ ኤንድ ፡ ፕሮሲጀር ፡ (ኒውዮርክ ፡ በብስ ፡ ሜሪል ፡ ኮምፓኒ ፡ ፲፱፻፶፩) ፡ ገጽ ፡ ፺፮-፺፫ ፡ የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ሕግ ፡ እንዳብራራው ፡ ዳግም ፡ ይኸው ፡ ተመሳሳይ ፡ ውጤት ፡ በኢጣልያንም ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ይመስላል ፡ (ዳይጀስት ፡ ኦፍ ፡ ኮሜርሺያል ፡ ሎውስ ፡ ኦፍ ፡ ዚ ፡ ወርልድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፺፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ይመለከቷል ፡) እንዲሁም ፡ በፒ ፡ ሩብየር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፭፬ ፡ እንዳብራራው ፡ በፍንቱም ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይኸው ፡ ውጤት ፡ ተገኝቷል ።

ቀዳሚነት ፡ ይኖረዋል ፡ በሌሎች ፡ ሕጎች ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ
የሆነው ፡ ያላስመዘገበው ፡ ወገን ፡ ቀደምትነቱን ፡ በሕግ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡(ለምሳሌ ፡
ለአምስት ፡ ዓመታት) ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ እንዲቆይ ፡ ይደረጋል ። በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ጊዜ ፡
ውስጥ ፡ እርምጃ ፡ በመውሰድ ፡ በኋላ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ወገን ፡ ምዝገባ ፡ካላስ
ፈቀደ ፡ በንግድ ፡ ምልክቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ሊያጣ ፡ ይችላል ።[77] በመጨረሻም ፡
አንዳንድ ፡ ሕጎች ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ ከማስመዝገብ ፡
ብቻ ፡ የሚመነጭ ፡ መሆኑንና ፡ አስመዝጋቢ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ሳያስመዘግብ ፡በቀደ
ምት ፡ ተጠቃሚ ፡ ከሆነው ፡ ወገን ፡ ይልቅ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ይናገራሉ ።[78]
ስለሆነም ፡ ምዝገባን ፡ ከመጀመሪያውም ፡ ሆነ ፡ ከችሮታው ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ወሳኝ ፡
ሁኔታ ፡ አድርገው ፡ የሚገምቱትም ፡ ሕጎች ፡ ቢሆኑ ፡ ሳያስመዘግብ ፡ በቀደምት ፡
ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ መብቶች ፡ በሙሉ ፡ ጨርሰው ፡ አያስቀሩም ። ለምሳሌም ፡
የፈረንሳዩ ፡ ሕግና ፡ በደንብ ፡ የታወቁ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችን ፡ በተመዘገቡ ፡ ምልክ
ቶች ፡ ወደሐሰት ፡ እንዳይለወጡ ፡ ምዝገባው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የተደረገ ፡ ከሆነ ፡ ለአ
ምስት ፡ ዓመት ፡ ካልሆነም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ይጠብቃቸዋል ።[79]
የካናዳው ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ "የተመዘገበውን ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ የተጠቀመበት ፡
ሰው ፡ ምልክቱን ፡ ያስመዘገበው ፡ (ምልክቱ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋለ ፡
ወይም ፡ የታወቀ) ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ከሆነ ፡ " የአምስት ፡ ዓመቱ ፡ የችሮታ ፡
ጊዜ ፡ ካለፈም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ የምዝገባውን ፡ መሠረዝ ፡ ይፈቅዳል ።[80]

ላልተመዘገቡ ፡ የንግድ ፡ ምልክቶች ፡ መብቶችን ፡ ከመስጠታቸውም ፡ በላይ ፡ ብዙ
ዎች ፡ ሕጎች ፡ ለተመዘገቡ ፡ ምልክቶች ፡ እርግጠኛ ፡ ሁኔታን ፡ ለማትረፍ ፡ ባቀዱት ፡
ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያልተመዘገበ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ባለቤት ፡ የሆነውንም ፡ ሰው ፡
ምልክቱን ፡ በመጠበቅ ፡ እንዲረዳበት ፡ አድርገዋል ፡ ይህም ፡ በምዝገባ ፡ ሹማምንት ፡
አማካይነት ለምዝገባ ፡ የቀረበው ፡ ምልክት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በቀደምት ፡ መዋሉ ፡
አለመዋሉን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚደረገውን ፡ ቁጥጥር ፡ ሊጨምር ፡ ይችላል ። ወይም ፡
ለምዝገባ የቀረበው ፡ ምልክት ፡ ሳይመዘገብ ፡ ወይም ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ በማስ

---

77. ለምሳሌም ፡ ትሬድ ፡ ማርክ ፡ አክት ፡ (ካናዳ) ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ ፩-፪ ኤሊዝ ፡ ፪ ፡ ምዕራፍ ፡ ፵፱ ፡ የዓይነት ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ። ቁጥር ፡ ፩ ፡ የ፲፱፻፴ ፡ የብሪቲሽ ፡ ትሬድ ፡ ማርክ ፡ አክት ፡ ቁጥሮች ፡ ፯፡፲፩ና ፡ ፲፫ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ድንጋጌ ፡ ያወዳድሯል ። በካናዳው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የችሮታው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ፍ/ቤቱ ፡ በአንዳንድ ፡ በተወሰኑ ፡ ሁኔ ታዎች ፡ ውስጥ ፡ ያልተመዘገበው ፡ ምልክት ፡ ከተመዘገበው ፡ ምልክት ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ሊፈቅድ ፡ ይችላል ። ቁጥር ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

78. ለምሳሌም ፡ ሎው ፡ አሻ ፡ ዲሴምበር ፡ ፴፩ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ፈረንሣይ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ (ሉ፡ ሻሻኝ ፡ በሩሲዬል ፡ ደሎዝ ፡ ሲሬይ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ክሮኒክ ፡ ገጽ ፡ ፪፫ ፡ ውስጥ ፡ ስለዚሁ ፡ሕግ፡ የሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ ይመለከቷል ። አርጀንቲን ፡ ሎው ፡ በዳይጀስት ፡ አፍ ፡ ኮሜርሽያል ፡ ሎውስ ፡ አፍ ፡ ዚ ፡ ወርልድ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፡ የተጠቀሰው ፡ ውስጥ ፡ እንደተብራራ ፡ ዳግም ፡ የጀርመንን ፡ ሕግ ፡ ይመለከቷል ። ያልበለጸጉ ፡ አገሮች ፡ ሞዴል ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ኢ. አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ የተጠቀሰው ፡ እንዳብራራው ፡ ያወዳድሯል ።

79. ሎው ፡ አፍ ፡ ዲሴምበር ፡ ፴፩ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ቁጥር ፡ ፬ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፩ ፡ የተጠቀሰውና ፡ የሉ ፡ሻሻኝ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፸፰ ፡ የተጠቀሰው ፡ አስተያየት ። ይህም ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ፈራሚዎቹ ፡ በዝርዝሩ ፡ መሠረት ፡ የታወቁ ፡ ምልክቶች ፡ እንዲጠብቁ ፡ የሚጠይቀውን ፡ የፓሪሱን ፡ ስምምነት ፡ ቁጥር ፡ ፮ለ ፡ መንፈስ ፡ የሚፈጸም ፡ ነው ።

80. ትሬድ ፡ ማርክ ፡ አክት ፡ ቁጥር ፡ ፲፯/ለ ፡ የዓይነት ፡ ሕግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ተመሳሳይ ፡ ውጤትን ፡ ያስከትላሉ ። ኢ. ፡ አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፮ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ያወዳድሯል ።

ታወቂያ ፡ ወጥቶ ፡ ሲያበቃ ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የመቃወም ፡ ወይም ፡ ምዝገባውን ፡ የማስሰረዝ ፡ ዕድል ፡ እንዲኖራቸው ፡ ይደረጋል ።[81]

በዚህ ፡ ክፍል ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ምዝገባ ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ ውስጥ ፡ በተለይም ፡ የተከሳሹን ፡ የአእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ በማረጋገጥ ፡ ረገድ ፡ አግባብነት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ ነበር ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ ተፃራሪ ፡ ሀሳብን ፡ ያመለክታል ፡ ይኸውም ፡ በኋላ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ በኩል ፡ የሚደርስበትን ፡ ኃላፊነት ፡ ምልክቱን ፡ መጀመሪያ ፡ በማስመዝገብ ፡ ሊያስወግድ ፡ መቻሉን ፡ ይገልጻል ። በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ምልክት ፡ ያልተመዘገበ ፡ እንደሆነ ፡ በኋላ ፡ ተጠቃሚ ፡ በሆነው ፡ ወገን ፡ በኩል ፡ መጥፎ ፡ ሕሊናም ፡ ሆነ ፡ ቸልተኛነት ፡ አለመኖሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይረዳል ። ስለሆነም ፡ አስመዝጋቢው ፡ ወገን ፡ በእርግጥ ፡ መጥፎ ፡ ሕሊና ፡ እንዳለው ፡ ወይም ፡ ቸልተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ጥበቃ ፡ የሚመለከቱ ፡ መመሪያዎች ፡ ተቀባይነት ፡ ካገኙ ፡ ምዝገባ ፡ ኃላፊነቱን ፡ ሊያስወግድለት ፡ አይገባም ።[82]

በምንነጋገርበት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሹ ፡ ምልክቱን ፡ ከማስመዝገቡ ፡ በፊት ፡ ስለከሣሹ ፡ ምልክት ፡ አጣርቶ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ።[83] ስለሆነም ፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ መሠረታዊ ፡ ነጥብ ፡ የምልክቶቹ ፡ ተመሳሳይነት ፡ መሳከርን ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ ዓይነት ፡ አይደለም ፡ የሚለው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሀሳብ ፡ ነው ። ይህም ፡ በማይገባ ፡ ውድድር ፡ በኩልና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷፩ ፡ መሠረት ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለውን ፡ ኃላፊነት ፡ ሊያስወግድ ፡ የሚችል ፡ ነው ፡ እንዲያውም ፡ ምልክቶቹ ፡ እስካልተመሳሰሉ ፡ ድረስ ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚው ፡ ክሱን ፡ የሚመሠርትበት ፡ ምክንያቱ ፡ እጅግ ፡ የመነመነ ፡ ስለሚሆን ፡ ምልክቱንም ፡ አስመዝግቦ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮም ፡ ኃላፊነት ፡ መወገዱ ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። እንዲህም ፡ ሆኖ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምዝገባን ፡ ራሱን ፡ እንደቻለ ፡ ጉዳይ ፡ አድርጎ ፡ ቢገምተውም ፡ ሳያስመዘግብ ፡ በቀደምት ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ምልክትና ፡ ያስመዘገበው ፡ ሰው ፡ ምልክት ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆነው ፡ አስመዝጋቢው ፡ ወገን ፡ ያስመዘገበው ፡ በመጥፎ ፡ ኅሊና ፡ የሆነበት ፡ ጉዳይ ፡ ቢገጥመው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ።

## ፬/ ስለማስታወቅ ፡

በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ሆነ ፡ በቀረው ፡ ዓለም ፡ በአንድ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ለመጠቀምና ፡ ምልክታቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ማስታወቂያውን ፡ አውጭ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ምልክትን ፡ ካለባቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ጋር ፡ በተያያዘ ፡ ጉዳይ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በንግዱ ፡ ምልክት ፡ እንዳይጠቀሙ ፡ በጋዜጣዎች ፡ "የማስጠንቀቂያ ፡ ማስታወቂያዎችን" ፡ በማውጣት ፡ ማስጠንቀቃቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ በማናቸውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እንዲሟላ ፡ አልተጠየቀም ፡

81. ኢ ፡ አፍነር ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጾች ፡ ፩፻፴፮ ፡ ያብራራውን ፡ በሞዴሉ ፡ የሕግ ፡ ረቂት ፡ የቀረቡትን ፡ የምዝገባ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያወዳድሯል ።
82. ይህም ፡ የንግድ ፡ ምልክቶችንና ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስሌዳዎችን ፡ በሚመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ውጤት ፡ የሚመስል ፡ ነው ። ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ ይመለከቷል ።
83. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፰ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍርድ ፡ አስተያየት ፡ ይመለከቷል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ መዋሉ ፡ በጣም ፡ የሚደገፍ ፡ ነው ። ማስታወቂያ ፡ ማውጣት ፡ የንግድ ፡ ምልክቱን ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያውቀው ፡ ከመርዳቱም ፡ በላይ ፡ ለሌሎች ፡ ነጋዴዎችም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ልምድ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ መብቶችን ፡ በሚመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠው ፡ የሚገባ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።[84]

## መደምደሚያ ፡

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ጥበቃ ፡ በተለይ ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ በሚመለከቱት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ (ቁጥሮች ፡ ፻፴፪-፻፴፮) ና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፳፬ ፡ ላይ ፡ የተመሰረተ ፡ ነው ። የንግድ ፡ ምልክቱ ፡ በንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ መመዝገብ ፡ ለጥበቃው ፡ በቀደምት ፡ ተሟልቶ ፡ መገኘት ፡ ያለበት ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ማስታወቂያዎችንም ፡ ማውጣት ፡ የተለመደ ፡ ነው ። የተለየ ፡ የንግድ ፡ ምልክት ፡ ሕግ ፡ መፈጠር ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ የተፀነሰ ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከት ፡ ሕግም ፡ በዝግጅት ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሕግ ፡ አሁን ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አሻሚ ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚያብራራውና ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ በዚሁ ፡ ሕግና ፡ አሁን ፡ የንግድ ፡ ምልክትን ፡ በሚመለከቱት ፡ የሕጉ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ እንደሚገልጸው ፡ ተስፋ ፡ ይደረጋል ።

---

84. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፸፫ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ የጠ.ን.ነ.ፍ/ቤት ፡ በአዛናው ፡ ዓለሚና ፡ በሲንጀር ፡ የስፌት ፡ መኪና ፡ ኩባንያ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የምዝገባውን ፡ ውጤት ፡ ሲመረምር ፡ በንግድ ፡ ምልክት ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ መጠቀምን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መሠረት ፡ እንዳደረገው ፡ ይገነዘቧል ።